በተኮላ መኮንን

tekolamekonen@yahoo.com

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | ገጽ 3 |
| 2 | ምስጋና | ገጽ 7 |
| 3 | መታሰቢያ | ገጽ 9 |
| 4 | አዲስ አበባ | ገጽ 10 |
| 5 | አሁንም ቢሆን ታጋይ ነኝ | ገጽ 14 |
| 6 | አድዋ | ገጽ 20 |
| 7 | ምንድነው እርጅና | ገጽ 22 |
| 8 | ስደት | ገጽ 24 |
| 9 | የማያድን ጀብ | ገጽ 27 |
| 10 | ፀጋዬ | ገጽ 29 |
| 11 | ማነው እሱ | ገጽ 32 |
| 12 | እንባዋ ውስጥ | ገጽ 35 |
| 13 | ምነው እማማ ጣርሽ በዛ | ገጽ 38 |
| 14 | እስቲ በልማቱ አንጣላ | ገጽ 40 |
| 15 | የኪነቱ ንጉሥ | ገጽ 43 |
| 16 | ካንቺ ከመጣ ኤርትራ | ገጽ 45 |
| 17 | ደብረብርሃን | ገጽ 46 |
| 18 | ለእሱ ብርታት | ገጽ 48 |
| 19 | የዘሩ ክሽን ስንብት | ገጽ 50 |
| 20 | ሚሊኒየም | ገጽ 52 |
| 21 | አሲምባ | ገጽ 55 |
| 22 | ሕጻንም ለካ ይሞታል | ገጽ 57 |
| 23 | እማማ | ገጽ 60 |
| 24 | ትእግስቱን አድለን | ገጽ 63 |
| 25 | ጓደኝነትሽን ላመስግን | ገጽ 67 |
| 26 | ደህና ሰንብት አበጀ | ገጽ 69 |
| 27 | ምነው ዳግም ጦርነት? | ገጽ 71 |
| 28 | ጉንፋን | ገጽ 74 |
| 29 | ሙስና | ገጽ 75 |
| 30 | ረሃብ ወይንስ ቸነፈር | ገጽ 76 |
| 31 | ለዲሞክራሲ እንታገል | ገጽ 77 |
| 32 | ዓባይ ደፈረሰ | ገጽ 80 |
| 33 | ዘመን | ገጽ 84 |
| 34 | ሕብስቱ | ገጽ 86 |
| 35 | ሥጋም በቁሙ ሲከዳ | ገጽ 88 |
| 36 | መገዘዝ | ገጽ 91 |
| 37 | ጦርነት | ገጽ 93 |
| 38 | የገደሏችሁም ሞቱ | ገጽ 94 |
| 39 | ለፋሲካው ምን ታረደ | ገጽ 96 |
| 40 | ዝምታህን ፈሩት | ገጽ 97 |
| 41 | ሰው ጠፋ | ገጽ 99 |
| 42 | ዓባይ ልገደብ አለ | ገጽ 100 |
| 43 | ሕግ በምህረት ሲሸፈን | ገጽ 102 |
| 44 | ለማረሱስ እደርሳለሁ | ገጽ 104 |
| 45 | የመውደድ ጋሬጣ | ገጽ 106 |

# መግቢያ

በየጊዜው የጻፍኳቸውን ግጥሞች በተለያየ ወቅትና ቦታ ላድማጭ ማቅረቤ ይታወሳል። የተፈለገውን ያክል ተዳርሷል ብሎ ማለት ግን ሃቅን መካድ ይሆናል። ስለሆነም ይህ የዛሬው የግጥም መደብሌ ከትላንትናው በተሻለ መንገድ ለአንባብያን ይዳረሳል ብዬ እገምታለሁ።

አንድ ገጣሚ ስሜቱ በተነካበት ሰዓት ያየውንና የታዘበውን፣ ባለፈ የተደረገውን፣ ወደፊት የሚተነብየውን አጠናቅሮ ለአንባቢ ወይንም ላዳማጭ ሲያቀርብ፥ በወቅቱ የተሰማውን ስሜት በመግላሊት እንደ ተከደነ ማሰሮ ታፍኖ ባልተፈለገበት ሰዓት እንዳይገነፍል መግላሊቱን ከፈት በማድረግ ለማስተንፈስ ጥረት ማድረጉ እንደሆነ መታሰብ ይኖርበታል። የገጣሚው ስሜት ለሁሉም አንድ ዓይነት ስሜትና ግንዛቤ ይሰጣል ባይባልም፣ ሁሉም ከራሱ እውቀትና ተመክሮ ጋር እያያያዘ፣ እያዛመደ በተቻለው ሁሉ የጸሐፊውን አባባል ሊረዳ ይሞክራል ማለት ነው። ከክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል ዋርዲትና ሸክሊት፣ ማራት አትአማራት፤ ከሎሬት ጸጋዬ ገብረምድህን የቴዎድሮስ ስንብት በመቅደላ፣ አይ መርካቶ ጭምር የተካተተው የአገራችን ግጥም በእነ አቶ ዮሐንስ አድማሱ የግጥም ሥራዎች እየታቀፈ የቆየውን የክቡር ብላታ ሕሩይ ወ/ስላሴ ወዳጄ ልቤን የሃይማኖት ስንኝ እየዳሰሰ በአቶ ሃይሉ ገ/ዬሐንስ በረከተ መርገም የቅስቀሳ ስላቅ ግጥም እያነሳሳ እነሆኝ ካለንበት ዘመን ደርሷል።



በአገራችን የነበሩ የኪነት ሰዎች ብዙዎቹ ሃይማኖት ላይ ያተኮሩ ውዳሴዎች ወንጌል አዘል ቅኔውች፣ ነገሥታትና ሊቃውንቶች ላይ ያነጣጠሩ ምስጋናዎች፣ በሰምና ወርቅ የተነገሩ አባባሎች፣ ከዚያም አልፎ የፍቅርን ውበት ለመግለጽ፣ ወኔን ለማነሳሳት፣ ጀግንነትን ለማሳየት ሁሉ የሚጠቀሙበት ግጥም እያደገና እየጎለመሰ የመጣው ከአብዮት ፍንዳታ በኋላ ለመሆኑ ስምምነት ላይ የሚደረስ ይመስለኛል። የሶሺያሊዝም ጠንካራ ጎኑ ደግሞ "ኪነትና ድህነት" ከማሳደጉ ላይ ነው እንዲሉ፣ በሃገራችንም የኪነት እድገት ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ በደርግ ዘመን መፍለቁን መካድ የሚቻል አይመስለኝም። በወቅቱ የተነሱ ደራስያን ላይ የነበረውን ጫናና ተጥሎባቸው የነበረውን ፈተና ስናስብ ደግሞ ለኪነት የከፈሉት የህይወት ዋጋ ቀላል እንዳልነበረ እንረዳለን።

የደርግ መንግሥት ተገርስሶ በወደቀበት ማግስት ደራስያን እንዳሸን ፈልተው፣ እንደ እንጉዳይ በቅለው በየቀኑ ለገበያ የሚቀርቡትን የእትምት ሥራዎችን ስንመለከት ደግሞ፣ ከትላንትናው የበለጠ ሆኖ እናገኘዋለን።

ዛሬ ባገራችን የዮፍታሔ ንጉሴን ስንኞች የማይደግም የፀጋዬን ግጥሞች በቃሉ የማያነበንብ ብዙ ወጣት ማግኘት ላይከብድ ይችላል። ይህ ደግሞ የደራሲዎቹ ያላሰለሰ ትግልና የሥራ ውጤት መሆኑ ነው። ሎሬንዝ ፀጋዬ ገብረመድህን ለተውኔት የሚሆኑ ጽሑፎችን ከመድረሳቸውም በላይ በተለያየ አዲስ የግጥም ምት የጻፏቸው ግጥሞች የራሳቸውን ስም መጠሪያ አድርገው

የፀጋዬ ቤት ተሰኝቶ የሚጠራ ድርብ ድርብርብ የቤት ግጥም ሲያበረክቱ፣ ያገራችንን የግጥም ግንዛቤና ይዘት ወደፊት አንድ እርምጃ ወስደውታል። የግጥሙ ለዛና ሃይል ብዙሃኑን እየቀሰቀሰ የማንበብና የማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርበት አድርጓል። ይኸው እኔም የተሰማኝን ለመጻፍ የበቃሁት ከነዚህ ደራስያን የሥራ ፍሬ በመቅሰም እንደሆነ ልናገር።

በስደት ዘመን በሱዳን ቆይታዬ አብረውኝ የነበሩት የስደት ወንድሞቼ ጭምር ብዙውን ጊዜ የምናሳልፈው የተለያዩ መጽሐፍትን በማንበብ፣ አጫጭር ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ በመጻፍና የተለያዩ ተውኔቶችን በመድረስ በመለማመድ ነበር። የነበረንን የጽሑፍ ፍቅር ተግባራዊ ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ጊዜአችንን በዚህ ላይ ማጥፋታችን ደግሞ ብዙ እንድንማር እንዳደረገን መናገር የሚያስደስት ነው እላለሁ። ከስደት በፊት ጽፌአቸው የነበሩትንና በቃል የማስታውሳቸውን ግጥሞቼን እንደገና በጽሑፍ ለማስቀረትም እድል የገጠመኝ በዚሁ የስደት ወቅት ነበር። ጽሑፎቼን በማንበብ ያበራቱኝ ከነበሩት ውስጥ እነ አቶ ሞት ባይኖር (ጃርሶ) ኪሩቤል፣ አቶ መስፍን ቀጸላ ይገኙበታል። ይህንን ማስታወስ ደግሞ ያለፈ ትዝታን መቀስቀስ ብቻ ሳይሆን ለሌላ የግጥም አርእስት መነሻም ሆኖኝ ቆይቷል። የአቶ ጌታቸው ቶሎሳን የማበረታቻ ቃላቶች የወይዘሮ ሶስና አድማሱን ድጋፍ ደግሞ ምን ግዜም የምረሳው አይሆንም። ብዙ ስሞችን መጥቀስ ሊኖርብኝ ነው። ጅምሬን እንዳላቆም ይገፋፉኝ የነበሩ በጣም ብዙዎች ነበሩና ሁሉንም ማንሳት የምችል አይመስለኝም። ባጠቃላይ ሁላችሁንም ይኸው የመጀመሪያውን ወረወርኩ ልበላችሁ።



“ኪነትን ከጦር መሳሪያ የበለጠ መጠቀም ይቻላል። መሳሪያ ያቆሰለው ሰው ሊያገግም ይችላል፡ በጽሑፍ የሚመሰገንና የሚነቀፍ ግን ቁስሉ እየቆየ ማመርቀዙ ውዳሴው እየሰነበተ ማበቡ አይቀርም” ይል የነበረው የአየር ወለድ አዛዥ የነበረው ኮሎኔል አለማየሁ አስፋው ነበር። ኮሎኔሉ የአየር ወለድ አዛዥ ሆኖ ሳለ ለምን “በእኛ ላይ አትቀልድም?” “ለምን ጽሑፎችህ በመሪዎች ላይ አያነጣጥርም? ተውኔቶቹም በጥሩ ሥራችን ላይ ሳይሆን በደካማ ጎናችን ላይ እንዲሆን አታደርግም?” ይለኝ ነበር። በትግራይ ሜዳ አብረን በቆየንበት ወቅትም ሆነ ወደ ኤርትራ ጉዞ ስንጀምር፣ ብሎም በኤርትራ የሽምሽምያ ቆይታችን እንገቱን የደፋውን ተጋዳይ ለማነቃቃት እስቲ አንድ ዝግጅት ፍጠሩ እያለ ሌት ከቀን ይገፋፋኝ ነበር። የእነ አቶ አንበርብር አበጀን (ኮሎኔል አለማየሁ አስፋውን) መስሎ መቅረብ የነከሰተ የተደበቀ ተሰጥኦ የነሂሩት (መዝገብነሽ) የፍቅር ግጥም ሁሉ ከዚያ የመነጨ እንደ ነበረ መናገር እችላለሁ። ይህም ወቅት የተለያዩ የተደበቁ ችሎታዎች ለአድማጭ የቀረበበት ወቅት ነበር። ብዙዎቹን ግጥሞች አሁንም አስታውሳቸዋለሁ። ከማስታውሳቸው አለፍ አለፍ እያልኩ ላካፍላችሁ?

የከሰተ

...............ጋሽ ጋሽ ጋሽ
በሁለት አብዮት መካከል ፈሳሽ
የከፋው እለት ዱቄት አጋጅ
ደስ ሲለው ግመል አራጅ

ከመዝገብነሽ

..... ዛሬም አልተለያየንም፣
ቃል ኪዳናችን አልተጣሰም፣
ዛሬም አልተነጣጠልን ትዳራችን አልፈረሰም።
የእንግዳ ቤት ነው እንደ ድሮው ቤታችን አልቀዘቀዘ፣
ጣራውም አላፈሰሰ ቀለሙም አልደበዘዘ።
ውድ ጓድ አልደብቅህም ብቸኝነት ግን ይሰማኛል፣
መልክህን ማየት እጓጓለሁ ስምህን መጥራት ያምረኛል።

ከአሰፋ
................ግራ ነፈሰ ነፈሰ
ቀኝ መለሰ መለሰ
እሳት ነደደ ነደደ
አመድ ተርኮሰ ተርኮሰ
እጅን ነከረ ነከረ
በጨርቅ አበሰ አበሰ
መሃበር ጠራ ጠራ
ወዲያው ፈረሰ ፈረሰ
እንዲህ አይደለም ወይ ፋሺዝም ሲነግሥ?

እነዚህ በትዝታ የማስታውሳቸው ናቸው። ያ የሽምሽምያ ቆይታ ተገባዶ ወደ ካርቱም ከተሰደድኩ በኋላ የጻርሶ "የአዲሳባ ልጆች" "ጋሼ ጉሉማ" "ዘብጥያ ቁጥር ሰምስት" "ጆርዳን" ............ ሲወለዱ የዓይን ምስክር ነበርኩ። የእኔም አባይ ደፈረሰ እንዲሁ እትብቱ የተበጠሰው በዚያው በካርቱም በከላአከላ ዛፍ ጥላ ሥር ነበር። በየጊዜው የጻፍኳቸውን ግጥሞች ይዘታቸውን ሳልቀይር የተውኳቸውም የነበርኩበትን እንዲያስታውሱኝ በማለት ነው። ስሞችንም እንዲሁ እንደ ነበሩ ትቻቼዋለሁ።



በተጨማሪም ቀደም ብሎ ከጻፍኩት ከውጥንቅጥ መጽሐፌ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግጥሞቼን እዚህም ወስጥ ደምሬአቸዋለሁ።

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ለአትምት የደረሰው ከጅምሩ እስከ መጨረሻው በባለቤቴ በወይዘሮ ማርታ አሰፋና ከወንድም በላይ በሆነው የዘመናት ጓደኛየ በአቶ ብንያም ጥላሁን ብርታት መሆኑንን መናገር እወዳለሁ።

ውድ ባለቤቴን ወይዘሮ ማርታ አሰፋን እንዴት ከተኮላ መኮንን ጋር ተጋብተሽ ትኖሪያለሽ? ላሏት ግለሰቦች የመለሰችውን ላካፍላችሁ። "የታወቀ ነገር የለም። ወይ እሱ ለእኔ መቀጫ ነው። ወይ እኔ ለሱ ምርቃት ነኝ።" የሚል ነበር። ለጓደኝነትሽ ክብር ይግባሽ፣ ላደረግሽልኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረስሽ፣ ለሰጠሽኝ ማበረታትና ድጋፍ ደግሞ አድናቆቴን ተቀበይ። ሕይወቴ ካላንቺ ትርጉም የለሽ ነውና።

የሲያትል ነዋሪ የሆነው ወንድሜ ብንያም ጥላሁን ያደረገልኝን እርዳታ ሁሉ መናገር ይከብደኛል። ከሳምንት በላይ ሳላወራው ከቆየሁ ትልቅ ነገር የጎደለ መምሰሉ ብቻ አይደለም ለማደርጋቸው ሁሉ መካሪዬና ድጋፍ ሰጪ ሆኖ በመቆየቱ አመስግኜው አላውቅምና ዛሬ የልብ ምስጋናዬን ባደባባይ ላቅርብለት። ብንያም የጓደኛ ትልቅነት የሚለካው በደስታ ጊዜ ብቻ አይደለምና እኔ እንዳንተ መሆን ባልችልም አንተ ግን ለኔ ከጓደኛ በላይ እንደሆንክ ልመስክር። አዲስ ጓደኛ ማፍራት ቀላል ነው የልብ ጓደኛ ማፍራትና ጠብቆ መኖር ግን ትልቅ ጥረትን ይጠይቃል። ታዲያ የኔና ያንተ ጓደኝነት ባንተ ብስለት እየተጠበቀ የሰነበተ በመሆኑ ምስጋናውን በሙሉ ላንተ ሰጥቼሃለሁና ተቀበለኝ።



በተጨማሪም በኮምፒውተር ችግር ሲገጥመኝም ሆነ ምክር ሲያስፈልገኝ ካጠገቤ በመሆን የረዳችኝ እህቴን ነፃነት ገብሩን ማመስገን እወዳለሁ። ነፃነት እንዳልሽው ችግሩ ከኮምቲውተሩ ሳይሆን ከእኔ ሊሆን ይችላል።

ለሕይወት ትርጉም እንዲኖረኝና ፍቅር እንዲያድርብኝ ያደረጉኝ በምንም የማልተካቸው ደግሞ ልጆቼ ናቸው። ቀልዳቸውን ሳልሰማ በሳቃቸው ብቻ እስቃለሁ። የሆኑትን ሳልጠይቃቸው በመከፋታቸው አለቅሳለሁ። የተናደድኩበትን ያስረሱኛል፣ በነሱ ፍቅር እንድኖር ሆኛለሁና። ዳግማዊ ተኮላ መኮንን ብስራት ተኮላ መኮንን አብይ ተኮላ መኮንን ሩት ተኮላ መኮንን ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ። በተለይ ሩት ሁል ጊዜ ማንበብ ስጀምርም ሆነ ከኮምቲውተር ፊት ስቀመጥ ምን ላምጣልህ የምትለኝን አልረሳውም። የ 8 ዓመት እድሜ ተመክሮዋ ከእድሜዋ በላይ አዋቂ አድርጓት ሳይ ደግሞ እጅጉን እገረማለሁ።

በተረፈ በማበረታታት ይህንን መደብል እንድጽፍ ያነሳሱኝን ሁሉ መጥቀስ ባልችልም እንኳን ሳልጠራ የማላልፋቸውን እንዳነሳ ፍቀዱልኝ። አቶ አዲሱ አሳምነውን፣ እህቴ በየነች መኮንን፣ ባለቤቷና ለእኔ ደግሞ የግል ጓደኛየን አቶ ስንታየሁ በዳሳን፣ አቶ ቢራቱ ዎዳንና ባለቤቱን ወይዘሮ ሰናይት አንባየን በዚህ አጋጣሚ ላመስግናችሁ። በናንተ ማበረታታት የመጀመሪያው ለአትምት ቀርቧል ለሚቀጥለው ደግሞ የእግዚአብሄር ፈቃድ ይጨመርበት።

## መታሰቢያ

**ይህ መጽሐፍ አብረውኝ ወደ ትግል ሜዳ ገብተው እንደ እኔ የመሰንበት እድል ላልገጠማቸው በትግል ላይ ለተሰው ቆራጥ የአየር ወለድ አባላት መታሰቢያ ይሁን።**



# አዲስ አበባ[1]

የጣይቱ የእውነት ሕልሟ፡ የምኒልክ እንቦቀቅላ፣
የመጤ ፍሬ ችግኝ ዛፏን ፥በዙሪያ አብቅላ፣
የአፍሪካ እምብርት ነኝ ብላ ኮርታ፡-የመሰብሰቢያ ዳስ
ጥላ፣
ፖለቲከኛ ለማኝ ላብ አደር፥ ሠራተኛውን ፈልፍላ፣
አሁንም አለች መኖር ካሉት፡- ስንቱን ጎበዝ አስኮብልላ።
አዲስ አበባ የትላንቷ፥ አዲስ አበባ  የሁሉ አድባር፤
ወና ሜዳው ጫካው ጎጥሽ ፍንፍኔ  ይባል እንዳልነበር፤
ያኔ በጠዋቱ የምኒልክ ጦር ሳይሰፍር።
ያኔ ገና የፈረንሳይ ባቡር ሳይገባ፣ አውሮፕላን ሳይዳስስሽ፤
ጋሪውም ሳይጎተት መኪና  ሳይፈነጭብሽ፤
ኩርኩር ሳትጀምር ፈረሰኛ ሳይዳምጥሽ፤
የነጭ ሰላቶ  ቆሻሻውን ሳይጥልብሽ፤
የቢኖ ጠርሙስ ሳይሰብርብሽ፥
ወደል አይጥ ሳይለቅብሽ።

ያኔ በልጅነትሽ የዛን ጊዜ  አዲስ አበባ፤
ጠረንሽ ሳይለውጥ ሙናሽ መቀመቅ ሳይገባ።
ከሶሪያ ነጋዴ ከአርመን ሽቃጮች ትምክህት፤
ከቱርክ ቸርቻሪ ከግብጥ ጳጳሳት በፊት።

---

[1] ከብዙ ዘመን የሰደት ኑሮ በኋላ የደርግ መንግስት ከስልጣንተባሮ አዲስ አበባን ተመልሼ ለመጎብኘት እድል ገጥሞኝ  በወቅቱ የጻፍኩት ግጥም። 10/30/1994

ቢትወደድ ፊት አውራሪሽ በዋርዳ ሲጋር በቅሎ፤
ወርቀ ዘቦ መደላድል ከግላሱ እናት ጥሎ፤
ፈረሱን በብር በነሃስ አሽሞንሙኖ፤
ካባ ለብሶ ነጠላ አደግድጎ፥ እንደ ጉብዝናው ተጀንኖ።

ያን ግዜ ባፍላነትሽ ያኔ በልጅነትሽ፤
ያኔ በሙሽራነት ያኔ በጫጉላነትሽ።
አዲስ አበባ አዲስ መንደር፤
አዲስ አበባ አዲስ ሰፈር፤
ድንበርሽ ሳይታወቅ፥ ገና በካሬ ሳይመተር፤
ከንቲባ ሳይሾምብሽ ቁጥቋጦሽ ሳይመነጠር።
እጅ መንሻ ሳትለምጂ፤
አራዳ ኡላ ሳትወልጅ።
ያኔ በድንግልናሽ፤
ሳይጠፋ ለዛ ሙስናሽ።

ያኔ እኮ ነው የምለው

ቦሌ ሳይመነጠር አስፋልቱ ሳይነጠፍ፤
ኮፍያ ደፋ ጦር ዘበኛ ሳይሰለፍ።
ተማሪ ሹራብ ሲሸለም የዱቄት ወተት ሲታደል፡
ወንጂ ስኳር ለናሙና ለወጣቱ ሲከፋፈል።

መርካቶ ነጋዴሽ ሲፈለፈል ገበያ አዳራሽሽ ሲሰፋ፤
የማሞ ካቻ አውቶቡስ ሲያናፋ።

ሚሊቼንቶ ሴቼንቶ ፊያት መንገድ ሲያቀና፡
ያኔ ነው የምልሽ ገና ወገብሽ ሳይጠና።



በኋላማ!!!

የልጅነት ልጅሽ አድጎ እንደ ቡሄ ሆያ ሆዮ፤
እንደ መስቀል አበባየ ሆይ ተው ስማኝ አገሬን ሲዘምር፤
ፋኖ ተሰማራን እያቅራራ የትግል ሀሁን ሲጀምር።
የካሳንችስ የለገሃር የአራት ኪሎ የዮሐንስ፣
የአባ ኮራን የጉለሌ የመርካቶ ሁሉ ጥንስስ፣
የቀበና የአቧሬ የአፍንጮ በር ወጣት ድግስ፣
የእንጦጦ ውቤ ሰፈር የሽሮ ሜዳ ትርምስ፣
የለገሃር የመድኃኒዓለም የቀጨኔ የጠዋት ጭስ።
የንፋስ ስልክ የኮልፌ የቦሌ የስድስት ኪሎ፣
ልጅ አዋቂው ተሰብስቦ መሬት ላራሹ ብሎ፣
ጆሊ የነበር ተለውጦ በልቧላ ሱሪውን ጥሎ፣
ሴቱም እንዲሁ ቆራጣ ቀሚስ አስጠቅልሎ፣
ላይደነክሩ ተገዝተው ሁሉም ባብዮት ስም ምሎ።

በአሸሽ ገዳዎ ምትክ የትግሉ ነው ሕይወቴን ዘምሮ፣
በፍልሚያው አምኖ በትግል ገመድ ተቋጥሮ።
ያንንማ ታሪክ አይረሳው!!
እሬሳ ሲሸጥብሽ ሰው እንደውሻ ሲጣልብሽ፣
የደርግ ፋሽዝም ሲነግስብሽ፣
ወጣት ልጅሽን ሲያርድብሽ።

ያኔ ሰው የረከሰበት ሰዓት፣
የተቃወመ ሁሉ የፋሽስት ጥይት ሲጋት፣
ጣረ ሞት ግቢሽን ሲያፍናት፣
መንገድሽን እሬሳ ሲሞላት፣
ማለፍ አይቀር አሳለፍሻት።

ዛሬም እልፍ አእላፍ አስተናግደሽ፣
በሰቆቃሽ ላይ ሰቆቃ ጥለሽ፣
የትናንቱን ለመርሳት ዳንኪረኛ ዘፋኝ ቀጥረሽ፣
የወጣት ኮማሪቶች አስመርቀሽ፣
በችግር መቀነት ታጥረሽ፣
የሰራሽውም ፈራርሶ፣
ቤትሽ ጣርያው አፍስሶ ።

መንገድሽ እንደ ጅብ ወጥመድ ከዚህ ከዚያ ተሰርጉዶ፣
ቆሻሻሽ  ተቆልሎ እንደ ደገኛ ነዶ።
ዛሬማ ዛሬማ!!
ገመምተኛ ነሽ እማማ!!
አዲስ አበባ አይ አዲስ አበባ!
የዮፍታሄ ውብ አሸከር ቀዘባ
አዲስ አበባ!!!!!



# [2]አሁንም ቢሆን ታጋይ ነኝ

ያደቆነ  ሰይጣን አይለቅ ቅስናውን ሳያከብር፤
ታጋይ ዓላማውን አይስት የጎተተውን ሳይቀብር፤
ያደናቀፈውን ሳይጠራርግ የገፋውን ሳያሽቀነጥር።
እናም አለን እንደ በፊቱ ከምናምንበት አልተንሸራተትን፤
በጥቅም ሳንደለል እውነትን ይዘን እየታገልን፤
የተሳሳቱትን ተጋፍጠን ሃሰቱን ሁሉ እያጋለጥን።
አለን አሁንም ታጥቀን የፍትሕ የእኩልነትን ዝናር፤
እየቃኘን እየገረፍን የዲሞክራሲን የመብት ከራር።
ትላንት የነበረውን በነገው እየተካነው፤
የተቀበረ የሞተውን በምኞት እያነሳነው፤
አለን አሁንም እንደ ትላንቱ ትግሉን እንደጨበጥነው፤
እረሃብን እየወጋነው፤
ድንቁርናን እያሳደድነው።

ጅምራችንማ!!

እንደ ባሕር ላይ አውሎ ነፋስ እንደ ደራሽ የጎርፍ ውሃ፤
እንደ ተለመጠ የደጋን እንጨት ብል እንደ በላው ቀርከሃ።
ተበተነ  ስብስቡ እንደ ገለባ በነነ፤
ዓለም በቃኝ እንዳለ መነኩሴ ገዳም ገብቶ መነነ።
ሞቶ እንደ ነበር እየረሳ በመኖሩ ተተበተበ፤

[2] በደርግ መንግሥት ላይ አምጸን የወጣንበትን 30 ዓመትበዳላስ ስናከብር ያነበብኩት ግጥም።
11/11/2010

የትግል ስሙን አሸቀንጥሮ
የናት ያባቱን ሲያስታውሰው፤
አልፏል እንጂ ተረስቷል የሚል ማን ነው?
በዚህስ ባለንበት ሃገር፤
የስደተኛው አኗኗር ለመሆኑ እንዴት ነበር?
እንዳልታገለ እየፈራ፤
ሥራ ሳይመርጥ እየሰራ።
ሁሉን በራሱ ጥረት በችግር ተማረበት፤
እዚህ የቆየው አበሻማ ሲያገኘው ድንገት፤
ስደተኛ በመሆኑ ተጠይፎት፤
እንደ ተላላፊ በሽታ ከሩቅ ቆሞ አሾፈበት፤
በባሌ መግባት ጀብድ እንዳልነበር
በቦሌ መውጣት ተኮራበት፤
በሱዳን ማለፍ ነውር ሆነና
"እኔ አላምንም" ተባባሉበት።
ታዲያ ብዙም ሳይቆዩ ስደተኛ
ለመሆን ገንዘባቸውን አፈሰሱበት
የናቁትን ስደተኛ ሊጋብቻ ተማጸኑበት።
አክብሩት ይህንን ታጋይ መከራ ያልተለየውን፤
በትግል በእምነቱ ጸንቶ ለፍሬ የበቃውን፤
ሀ ብሎ የተማረውን
ዛሬ የሚያስተምረውን፤
ዘመድ አዝማድ የረዳውን
ቤተሰብ ያስመጣውን፤
በሱ ትግል በሱ ብርታት
ኑሮን ያቀለለውን፤
ላዲስ መጪው መካሪውን
ያኗኗር ዘይቤ ጠቋሚውን።
ክብር ይግባው ለዚህ ተጋዳይ



ለመጭው ሁሉ መንገዱን ለቀደደ፤
ብረት ይዞ ለተዋጋ ለሰላም ለተሰደደ፤
በሱ ብስራት በሱ ዱካ ምልአተ ሕዝብ ለወለደ።
ወንድሞቼ ያ ሁሉ ጊዜ አልፎ ትላንት ለዛሬ ደረሰ፤
ያ ስደተኛ ወጣት በእድሜ በረከት ጸጋን ብርታትን
ተላበሰ።
ይህንን ያላጤኑ መጤዎች ሽበት እድሜውን አይተው፤
ሲሳለቁ ያስቀኛል ሃብትን መለኪያ አድርገው።
መስንበቱ ሳይገርማቸው ለዚህ እድሜ መብቃቱ፡
ሲያፌዙበት ያሳዝነኛል ገንዘብ ንብረት ባለማፍራቱ።
እኛ ታጋይ ነን ትላንትናም ታጋይ ነን ዛሬም ወደፊት፤
አንደበቅ ወራት ሲቀየር እንደ ሐምሌ ያገር ቤት
ጭልፊት።
የሚገርመን ዘንድሮ የማይዋጥልን ለመስማት፤
የድል አጥቢያ ታጋይ ሁሉ የኛን መፋለም ሲያንኳስሳት፤
መድማታችንን ሲያቃልለው መሞታችንን ሲቀልድባት፤
ጋን እልቆ ምንቸት የሆነው ታሪካችንን ሲያራክሳት፤
ገዳይ ሹንባሹ አንቱ ሊባል የኛን አንገት ሊያስጎነብሳት፤
የገረፈው ሊሸለም የገደለው ወንጀሉ ሲፋቅ፤
ዝም በማለታችን ፈርተዋል ተብሎ ሲሳቅ።
የሚገርመኝ!!
ከገዳይ ግንባር ገጥሞ እታገላለሁ የሚል ቡድን፤
የተሰደደውን የጥንት ተጋዳይ ለማጥፋት ባንድ ሲቦድን።
በስም ብቻ የሚኩራራ፤
እግሩ ፈንገስ ያላደራ፤
ወይ ዘብጥያ ያልወረደ፤
በወፌ ይላላ ያላበደ፤
ቅስቀሳ ያላካሄደ፤
አንቱ ሲባል ታጋዩን ስላዋረደ።

ጥይት ያልጮኸበት አዋጊ፣
ባየር ስልጣን ፈላጊ፤
ፋሽስት ለነበር አደግዳጊ።
እኛን ሊተች ሲነሳ ያናድደናል ከምር፤
አንዳችም ለትግሉ ሳይገብር፤
አንቱ ተብሎ ሲያጭበረብር።
አለን እስካሁን ወንድሞቼ ለምስክርነት ሰንብተን፤
ሳናስበው ለዛሬ በቅተን
በተመክሮ  በስለን፤
ቀልዳችን ለሌላው አይጥም ወሬያችን ለኛ አይሰለቸን፤
ምን ብንለያይ ለዓመታት እንደ ዘመድ ተነፋፍቀን፤
ጎጆ እንደ ወጣ የቤት ልጅ እንዴት ሆነ? ተባብለን፤
የስደት ዘምኑን በመሰረዝ ዛሬም ጎረምሳ ነን ብለን፤
እርጅናውን ሳንቀበል የወጣት ፈገግታ ሰቀን፤
የተሰውቱን እየጠራን፣
በትዝታ ከልባችን አስቀምጠን፤
የሞቱበትን ዓላም የገድል ሥራቸውን አከብረን፤
የዛሬ ፴ ዓመቱን እንደትላንት ቆጥረን፤
አለን ዛሬም በሕይወት ትግል በፈተና ተወጥረን፤
ምን ብንለያይ በሃሳብ አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ
ተባብለን።
አለን እንኖራለን ለወደፊት ባደረግነው ሁሉ ኮርተን፤
ኑሮን በጸጋ ተቀብለን፣
በኩልነት ተከባብረን፤
አለን ዛሬም እንደትላንቱ የሕይወት ታጋይ ሆነን።
አለን ባመጽ፤
መቃብራችን እስኪታነጽ።



# አድዋ

አድዋ  የደም እንባ አድዋ  የነፃነት በር፣
አድዋ የታሪክ ቀደምት የመጤ እሬሳ ከምር፤
የወራሪ ቅስም ሰባሪ፣
ጣልያን ሰላቶ አስገባሪ፤
የነጭ ኩራት የከሰመበት፣
ውኃ እንደ መድፍ የተዋጋበት፣
ጎራዴ ቀለሙ የቀየረበት፣
የፈረስ ኮቴ ጠላትን የጋለበበት።
አድዋ የፈረንጅ ቁስል፣
የማይጠፋ የማይከስል፣
ዓመት ከዓመት የሚመግል።
እንደ ሰነበተ ነቀርሳ፣
ውሎ አድሮ የማይረሳ፣
እያገረሸ የሚያስከሳ፣
ወገንን እያኮራ ጠላትን እጅ የሚያስነሳ።
አድዋ የጥቁር ኩራት፣
የምኒልህ የጣይቱ ብስለት።
ያባ ዳምጠው ያባ በለው፣
ያባ መቻል ያባ ቃኘው።
አድዋ ንግርት፣
አድዋ ትምክህት፣
የተናቀ የገነነበት፣
ያበጠ የፈናዳበት፣
ጀግና የፎከረበት፣
ጣልያን ያለቀሰበት፣
ባንዳ በቁሙ የሞተበት።

አድዋ የነፃነት ጮራ፣
ታሪክ በደም ተሠራ፣
ጀብድህ በዓለም ተወራ፣
ጅምርህ በአፍሪካ ተዘራ።
ከየት መጣ ጉልበቱ?
ጎራዴ ለጥይቱ፣
ጦር ሰብቆ ለጠላቱ፤
መሳሪያ ሳይሆን ቆራጥነት፣
ጥራት ሳይሆን የውጊያ ድፍረት፣
መድፍ ሳይሆን እንቢኝ ባይነት፣
ፈረስ ሳይሆን የእግረኛው ስምረት፣
ምሽግ ሳይሆን መስዋእትነት።
ታሪክ ሲሠራ በጥቁር ሰፈር፣
በነጭ ደም ድጓ ሲቀመር፣
ወራሪ እንደ ሌባ ሲባረር፣
አድዋ አበራ የድል ጀንበር።
ማነው ዛሬ ባሪያ እሚለኝ?
እኔም ባገሬ የነጭ ምርኮኛ ነበረኝ፣
በሰፈሬ የነጭ ሎሌ ነበረኝ፣
በስልጣኔው በሉ እንጂ
ታሪከስ እንደ እነሱ አልቸገረኝ፣
ምን ብጎሳቆል በኑሮ ለታሪክማ አድዋ አለኝ፣
የጥቁር ግሥላ የሚያሰኘኝ፣
ለክብሬና ለጀግንነቱ አሁንም የትላንትናው አድዋ አለኝ።



# ምንድነው እርጅና?

የእድሜ ጉልላት እንዳለው አሜጋው እንደሚታወቅ፣
ዓመት በዞረ ቁጥር እኔ እንደሁ አልሸማቀቅ።
እኔ አላምንም በማርጀት አልቀበልም በቀላል፣
እንደ ፍቅር እንደ ቁርሾ ወሳኝ ልብ ነው ይሏል።
ልቤ እኮ እንገር ነው ያልተነካ ጎረምሳ፣
እንደ አነር ተር ብሎ እሚሮጥ እንደ አንበሳ የሚያገሳ፣
ሳልሞከረው ከሩቅም ሆኖ ኩንታል እህል የሚያነሳ።
እንደ እባብ የሚተጣጠፍ ወገብ፥
እንደ ንስር አሞራ የሚያማትር እይታ፣
እንደ ገደል ላይ ሚዳቋ ጆሮ የሚያዳምጥ ጆት ኮሽታ።
ከያዘ የማይለቅ መዳፍ፥ ያየውን የማይረሳ አእምሮ፣
ቦታ የለውም ከኔ ዘንድ ማርጀት ይኸ ሁሉ ተደምሮ።
ትእግስተኛ ነኝ ያለወትሮ ማዳምጥ እንዳዲስ ጠባይ፣
ማስታረቅ ያስደስተኛል የተጣላ ሲተቃቀፍ ሳይ።
ይኸ ሁሉ የእርጅና ምልክት ነው ካላችሁ
እርጅና አልገባኝም ልበል፣
መጨመት እውቀት ነውና
ከስህተት መማሬን ልቀበል።
መጨመትም ሽምግልና ነው ካላችሁ፣
ወጣቱ ማነው እባካችሁ?
አጋጥሙኝ ከወጣቱ ይጠይቀኝ ልፈትነው፣
ከረታኝ አይሆንም እንጂ እውነት ብዬ ልቀበለው።
ከተረታ አረጀህ ላይለኝ ሰከነሃል ብሎ ሊቀበለኝ፣
በሰልክ ብሎ ሊናገር ጨመትክ ብሎ ሊያከብረኝ፣
ከተመከሮዬ ሊጋራ የታየውን ሊያካፍለኝ፣
እርጅና የለም ውሸት ነው እድሜ ቁጥር ነው ሊለኝ፣

ከተስማማ ደስ ይለኛል እኔ  ከቃሉ ጥል የለኝ፣
የተከመረ እውቀት ያለው ጎረምሳ ወጠምሻ ነኝ፥
ማነው ጀግና  እኔን አረጀህ የሚለኝ።



# ስደት[3]

SEATTLE, WA

የተከፋን ማጽናናት የቆረጠውን ለመመለስ መሞከር፣
ያመረረን ተወው ማለት ከታጠቀ መከራከር።
ከነቃ  በኋላ ተኛ ማለት ጉዞ  የጀመረን ማደናቀፍ፣
የተቀመጠው የቆመውን ትቶ የሚሮጠውን መተናነቅ
ለማቀፍ።
እንቢኝ ያለውን ይቅርብህ ብሎ መነታረክ፣
ችፌ ቁስሉን አለፍ ብሎ ያልበላውን ጎን ማከክ።
ያየውን አላየህም ብሎ መካድ
የሰማውን እንዳልሰማ  ማስመሰል፣
የተጣደውን ችላ ብሎ የተዘፈዘፈውን ማማሰል።
ይኸ ነበር ችግሩ መደማመጥ የጠፋበት፣
እየከረመ ሳይታወቅ ድንገት የፈነዳበት።
ያንተን ስለማላውቅ ጉዞህን
ብዙ ማውራት ይከብደኛል፣
ሮ ባ  ወንድሜ  ሙት እንኳን መጥለፍ ነፋሪትን
መሳፈሩም ያስፈራኛል።
እድሜህንም አልጠይቅህ እነ አራፋት ሲያረጁ ሳይ፣
ኮለጅ ተማሪ ነበርክ ልበል በታህሳስ በነገርማሜ ንዋይ?
በቅርብ የሚያውቅህ እንዳወራን ጣልያን በገባ በሳምንቱ፣
ጀመረ ይለናል የናትህ ምጥ ግፊቱ፣
የሕዳር በሽታ ቀን መቁጠሪያህ የሰገሌ ጦርነት ምልክቱ፣

3 ሲያትል ዋሽንግቶን ተደርጎ  በነበረው ስብሰባ  ላይ ጓድ አሮባን (አብዲሳን)  በሽለምነው ወቅት የተገጠመ  ግጥም።

ስንት እንደሆነ ታውቃለህ ቢደማመር ስሌቱ።
እድሜ  እኮ ታሪክ አይደለም መሰንበት እኮ ቆይታ ነው፣
ታሪክ ማለት ባሕር ዳር ሄዶ አውሮፕላኑን መጥለፉ ነው።
ቀልድ ነው ባትለኝ ዛሬ  አንተና  ጓደኞችህ ስትጠልፉ፣
ብዙዎች እንደ ነበሩ አትርሳ  ባውሮፕላን ሥር ያላለፉ።
ለምን? ብዬ አልጠይቅህ በትዝታ ትዘፈቃለህ፣
ካልጠፋ አረብ አገር አልል የነበረውን ታውቃለህ።
የምጠይቅህ የማልተውው ይኸ ድፍረት ካልሆነ?
ለምን አላሸነፍንም ብዬ ነው ለምን ታጋዩ ተበተነ?
ካልመሰለህ  አትናገር ዝምታ ወርቅ ነው ካልከን፣
ፍቅራችን ግን እንዳለ ነው ለጠባይህ ተገዝተን፣
በእኩልነት መነጽርህ በቅን ልቦናህ ተነክተን።
አሁንማ በወጣትነት የቀረብህን፣
በስተርጅና ልትወጣ ቁጭትህን።
ያባትህን ምኞት ሞላህ ይኸው ማንጁሶች አደረስክ፣
ሚዜ ሆነህ ለጓዶች ሰርግ ከዋና ከተማችን ወረድክ።
ትጥቅ ኩፉፉ ቢጠፋ ትተኸው ብትወጣ ካገር ቤት፣
ካሜራ ታጠቅህ አሉኝ የታሪክ ቅሪት ልትቀርጽበት።
እኔ ያለብኝ ችግር ያጋጠመኝ መከራ፣
አላምን ማለቱ ሰው ሁሉ አዋጊዬ ነበር ብዬ ሳወራ።
የትናንትናው አማጭ ተጋዳይ የትናንትናው የጦር መሪ፣
ፍርሃት የሌለው በረኸኛ ወጣት አዛውንቱን አክባሪ።
ዳግም ሳገኝህ የገረመኝ ለቀድሞ ጓዶች ያማሁህ፣
ፈገግታ ፍቅሩን ሳይሆን ስድቧንም አለመተውህ።
እንኳን ለዚህ ቀን አበቃህ በህይወት አብረን ልንቀመጥ፣
እንደ ጅምሩ ቢሆንማ ኖሮ ከሩቅ ሰላምታ ልንሰጣጥ።



ውድ እሮባ

ለቅንነትህ ጎንበስ ልበል ለጓድ ፍቅርህም ልስገድ፣
ለምስክርነት ሰንብትልን ዳግም ከእንግዲህ አንሰደድ።
ጓድ እንበልህ ካልተቆጣህ እንደ ጤፍ ዘር ተበትነን፣
ተገናኝተን እናውራ ጥፋ ከፊቴ ሃጠ.. ተባብለን።
እንኳን ደስ አለህ በዛሬው በሠራህበት ኩራበት፣
በቅሬታህ ሱባኤ ግባ መጭውን ግን ተጠቀምበት።

# የማያድን ጅብ በሬሳ ላይ ይበረታል

አቶ አሰፋ  ጨቦ በኢትኦጵ መጽሔት ዘሩ ከሸን ላይ ለጻፉት ፈጠራ ታሪክ የተሰጠ ምላሽ

እርግጫው ቢያስቸግራቸው በቅርበት ሆነው ቢያገኙት፣
አህያውን እራቅ አሉና ጭነቱን በሽመል መቱት።
እኔ ደራሲ እወዳለሁ የልቡን በጽሑፍ የሚናገር፣
እኔ ሠዓሊ አደንቃለሁ በቡሩሽ የሚከራከር፣
እኔ የኪነት ሰው አፈቅራለሁ በመሳሪያው የሚመከር።
እኔ ፖለቲከኛ አደንቃለሁ በሠራው የሚኮራ፣
በጥፋቱ የሚጸጸት ሂስ ግለሂስ የማይፈራ።
የማይዋጥልኝ አስመሳይ ጸታውን ያልለየ ዳንዴ፣
ደስ ሲለው ተጋዳይ ዘራፍ ባይ ባለ ጎራዴ።
ጠመም ሲል ሃይማኖተኛ ቆብ ያልደፋ መነኩሴ።
ጠብ መንጃ ያልጨበጠ ወታደር፣
ስላለፈው ውጊያ የሚናገር፣
ስለ መጭው ግድ የሌለው፣ ቀውጢ ቢመጣ የማይሸበር።
የሞቱትን የሚኮንን ምስክሮችን የሚከድ፣
ትርፍ ከተገኘበት በነፍሳቸው የሚነግድ።
ካልነበረበት ነበርኩ የሚል ካልዋለበት የሚውል፣
የደገፈውን የሚተክል የጠላውን የሚነቅል።
የታገለውን የሚያንኳስስ የራሱን ገድል የሚከምር፣
በፈጠረው ውሸት ተወናብዶ በመደጋገሙ የሚሰክር።
የዋሸውን ፈጠራ እየረሳ፣
እመኑኝ ብሎ የሚያገሳ።
ዘንድሮስ በዛ ሃሰት ውሸቱ ገደብ አጣ፣
ጋን ጋኑ አለቀና ማሰሮው ከማጀት ወጣ።
አቶ አሰፋ ጨቦ ከሰሙኝ የመስማት ችግር አለብዎ:



ተጋዳይ አልነበሩ አይደሉም ሕሊናዎ ይውቀስዎ።
በሞት ያለፈን ተጋዳይ ሊሳለቁበት ሲነሱ፣
እምነቱን ሲያዳድፉበት ጥንካሬውን ሲያንኳስሱ።
ዘሩን በዘሩ ሲፈርጁበት ዘረኛ አይደለሁም እያሉ፣
ጀብዱ ከመሰለዎ በእውነት ወንድሜ ተታለሉ።
ምክንያቱ ግራ ቢያጋባም መታሰርዎን አውቃለሁ፣
ለኢጭአት መፈጠር ሚና እንደ ነበረዎት እሰማለሁ፣
ከመኤሶን ጋር እንደ ተጋቡ የሊቀመንበሩ ጡት
ልጅ እንደ ነበሩም ሰምቻለሁ።
ታዲያ  እርስዎም  በወቅቱ ኮሚኒዝም ጭቁን ሕዝብ
እንዳላሉ፣
ከነበረው ሞቅ ሞቅ አብረው እንዳልፎለሉ፣
በተጋደሉት ሊቀልዱ ሌላ ሰው መስለው ሊያታልሉ?
ጠበቃዎች በፍርድ ቤት የተለየ ምስክርነት የሰጠን ሰው፣
ለዳኛው ለማጋላጥ ጥርጣሬን ለመተው፣
የቱን እንቀበለው ብለው ይጠይቃሉ?
የፊት ቃሉን ወይንስ የአሁኑን?
የዋሸው ጠዋት ሲነግረን?
ወይስ ማምሻውን ሲተርከን?
ታዲያ የእርሶም ለሰሚ ከበደ፣
ነግሼ ነበር አይሉ ወይ ዘውድዎ አልወረደ።
አምናለሁ ባሉት አልጸኑ ወይ ግለ ሂስ አላካሄዱ፣
ሁኔታዎች ሲቀያየሩ በብእርዎ ተወናበዱ።
በፈጠሩት ውሸት ተታለው እርስዎም ግራ ተጋብተው፣
እኛንም ግራ ሊያጋቡን ሞከሩ
መያዣ መጨበጭያ አሳጥተው።
ይስከኑ አቶ አሰፋ የሰከነ ይበጃል፣
እምነት ያጣ አስተሳሰብ ከእድሜ ቀድሞ ያረጃል፣
ውሸት የሞላው ሕሊና እውነት ሳይጥመው ይጃጃል።

# ፀጋዬ

እንደ ገዳም ትልቅ ዋርካ፣
እንደ እሚያስፈራ የነብር ዱካ።
እንደ ወደቀ ትልቅ ዘንዶ፣
ያየው ላካልህ ሰግዶ።
ጣትህ እንደ አዳኝ የጦር ብእር ሰብቆ፣
ለቅሶህ ከደስታ ተጨምቆ።
ሰቆቃህን አሰምተህ፣
ወኔ ጀግንነትን ቀስቅሰህ፣
የቴዎድሮስን እንባ አንብተህ፣
የጴጥሮስን መስቀል ተሳልመህ፣
ፍርሃቱን ገልጠህ፣
ግዝት እርግማኑን አስተምረህ፣
እነ ኦቴሎን ደቅለህ፣
ባዲስ ቋንቋ አስለፍልፈህ፣
እነማክቤትን ላገራችን ጉዲፈቻ አስጥተህ፣
"ሀ" ብለህ "ሁ" ብለህ አቡጊዳን ዘምረህ።
የረሃብን ቀን በመቁጠር ያለፍከውን መንገደኛ፣
"የማውቅህ የማታውቀኝ" ያልከው ዳኛ፣
ዛሬ እንደ ቀልድ ልትተኛ?
አይ መርካቶ አይ መርካቶ፣
ምን አለ ይሆን ፀጋዬን አጥቶ?
ፀጋዬ ባለቅኔ ፀጋዬ የመድረክ ሰው፣
ስንቱን ፈጠርከ ስንቱን እስትንፋስ ሰጠኸው!!!!
ለስንቱ ታመምክ የስንቱን በር አንኳኳኸው፣
ወጣቱን የግጥም ብእር አስጨበጥከው።



ፀጋዬ የአገር አድባር
ፀጋዬ የኪነት ምግባር፣
ፀጋዬ የግጥም ምሰሶ
ፀጋዬ የተውኔት ምስማር።
በአካልስ አላውቅህም
ስላንተ ግን አወራለሁ፣
ሞትህም አላገደኝ በሥራህ አንተን አይሃለሁ።
የብእር ነጠብጣብህ ግጥምህን እንደ ሰሞነኛ ቁስ ስደግም፣
ቅኔህን ስዘርፍ እንደ ሕፃን ጡት ጠቢ ሳጣጥም።
እንደ እንቦሳ ስፈነጥዝ እንደ እረሃብተኛ ሳቀረቅር፣
ሥራህን ስተነትን እንደ ወፍጮ ቤት ጤፍ ሳበጥር።
እሰየው በርታ ሳልልህ ሞተ አሉኝ፣
ማሸለብህን አረዱኝ።
ሎሬት ይሉሃል ፈረንጆቹ
ሊቀ ጠበብት ማለት ፈልገው፣
በጥናትህ ተገርመው፣
በሥራ ውጤትህ ተሸብረው።
"ምን ታምር እንስራ ወንድሞች ታሪክ ያላየው ሃቅ የለም፣
"
ከሜካ ተዘርቶ አይበቅል ፀጋዬ እጽዋት አይደለም።
እናም ወንድሞች ተጠናከሩ፣
የፀጋዬን ምግባር ዘክሩ፣
ባለቅኔው አንቀላፍቷል ብላችሁ ተናገሩ።
አዋሽ አሰማ ብሶትህን፣
ዓባይ አንቆርቁር እንባህን።
አንቺም እማማ አልቅሺ
መቼም ማልቀስ እርግማንሽ፣
ሽማግሌ ላይቆይብሽ
የሚያስብልሽ ላይከርምብሽ።

የሚጦርሽ ሊቀጭብሽ፣
አቦካቶሽ ሊረታብሽ፣
ምን አልሽ ፀጋዬ እኮ ተኛ ሲሉሽ?
ማንቀላፋቱ ካልቀረ
ያንድ ወጥ መንገድ ከጀመረ፣
ለሌላ ኃይል ብናስረክበው
ሥራው አልተቀበረ።
ወላዲት አምላክ ፀጋዬ ወደ አንቺ ጋ ከመጣ፣
ነፍሱ ከበለጠበት ድኩም ስጋውን ካጣ።
እፍ በይበት ትንፋሽሽን አትንፈጊው፣
ትር ብር እንዲል አክናፍሽን አልብሽው፣
ፍርሃቱን ግፈፊለት አንቺ መጠለያ ሁኚው።



# ማነው እሱ ኢትዮጵያዊ

05/02/2006

እንቡር የሚል እንደ ጥጃ፦ እንደ ፍልፈል አፈር ወዳጅ፣
እንደ ግልገል የሚፈነጭ :- ሽር የሌለው ሁሉን ለማጅ፣
እሱ በቆሎ እያደረ፦ ለእንግዶቹ ጠቦት አራጅ።
እትብቱን በምድሯ የቀበረ ወላጆቹን የሚናፍቅ፣
ለወደቀው ደረት ደቂ ለደስታው የሚፈነድቅ፣
ለጓደኛው የሚንሰፈሰፍ ዘመድ አዝማድ የሚጠይቅ።
ማነው እሱ ኢትዮጵያዊ? የትኛው ነው ባለገሩ፣
የከተማው መምህር ነጋዴ ወይስ አፈር ገፊው ገባሩ።
ማነው ኢትዮጵያዊ እባካችሁ?
ነገር ታሪክ የሞላችሁ፣
ንገሩን እንስማችሁ።
የተዋጋ ላገር ድንበር፣
የተዋደቀ ወታደር፣
ወይስ ብእር ይዞ የሚተርክ ስለ መብት የሚከራከር?
መነኩሴ ይሆን ቆብ የደፋ ካልሆነ ሰሞነኛ ቄስ?
የሚራወጥ ከተዝካር ቤት ከነጌቶቹ ድግስ?
ስልጣን ያናወዘው ፖለቲከኛ፣
ሽር እያሰበ የማይተኛ፣
የመንዝ ደበሎ ለባሽ የዶርዜ ጠበብተኛ?
ማነው ወንድሞች አገር ወዳዱ?
የቱ ነው እሱ ኢትዮጵያዊ?
ለሰማይ ቤቱ የሚያስብ ነፍሱን የረሳ ዓለማዊ።
ኦሮሞ ይሆን ሲዳማ ገሙ ይሆን ወላይታ?
አፋር ነው አባ ዘላን ኢሳ ነው ወይንስ ከንባታ?

ሐረሬ  ነው የሚኮራባት?
ጉራጌ ነው የንግድ አባት?
ሱማሌ ይሆን የአዋሽ ውልዱ?
ትግራይ ነው እንዴ ነገዱ?
ሺናሽን ይሆን ሻንቅላ?
የጣሊያን የግሪክ ዲቃላ?
አማራ ነው ቅማንቴ?
ጎንደሬ ነው ወልቃይቴ?
ክርስቲያን ይሆን እስላም?
ጎረምሳ ካልጋ የዋለ ሕማም?
እስከ እማውቀው እኔ  እንደገባኝ፣
ከበርቴው ያገር ዲታ አርሶ አደር አፈር ዘጋኝ፣
ላሊበላ ወዮ ዓለም ባይ ቤት የሌለው የጠዋት ለማኝ፣
ሠራተኛ ላብ አደር ተማሪ ያገር ሸንጎ ተመራጭ፣
ፍትሐ ሰጪ ከወንበር ላይ በሰው ቁስል ፈራጅ ቆራጭ።
በኢትዮጵያ ከርሰ ተፀንሶ በምድሯ የተወለደ፣
በእናትነቷ የሚኮራ በድህነቷ ያልተዋረደ።
በጭቃ  የተጫወተ ባልጋ  በመደብ ያደገ፣
ዳስ ጥሎ ሰርግ ያበላ ለለቅሶ ያደገደገ።
ከበግ ከከብት ተሻሽቶ ጠረን ትንፋሽ የለመደ፣
ለአባት ለእናቱ ለጎረቤት ያጎበደደ።
ከሼህ ከቄሱ የሚደበቅ፣
ሽማግሌ የሚያከብር፥ በሃዘኑ የሚሰቀቅ፣
ለራሱ ሳይሆን፥ ለሌላው ችግር የሚጨነቅ።
ኢትዮጵያዊ ነው፥የምለው በእዛች ሃገር፣
ለእኩልነት የሚቆም፥ ለዲሞክራሲ የሚከራከር፣
የሌላውን መብት ያከበር በመብቱ የማይደራደር፣
ላገር ልእልና ቆሞ ፥ዳር ድንበሯን የሚያስከብር።
ኢትዮጵያ  እናቱ መሆኗን ያመነ፣



ለስሟ ደህንነት ቆሞ የታሰረ የመነነ፣
ደግ ጎኗን አጠናክሮ ገበናዋን የሸፈነ፣
መቃብሯን ያልቆፈረ ቁስል ስብራቷን የጠገነ፣
የፈራረሰውን የሚገነባ የተከፈተውን የከደነ።
ለሌላው ጥብቅና ቋሚ፣
የሕዝብ ብሶት የሚገባው ልዩነትን አስታማሚ።
በስልጣን ቅዠት ያልታነቀ በዜግነቱ የሚኮራ፣
የፍትሕ ችግኝ የሚተክል የእኩልነት ዘር የሚዘራ።
እሱን ነው ኢትዮጵያዊ የምለው፣በብእሩ ለሚፋለመው፣
በሙያው ለሚራወጠው፣
ላቡ ለሚንጠፈጠፈው፣
ሕልሙ እድገቷ ለሆነው።

# እንባዋ ውስጥ ሲቀመጥ[4]

ከፖለቲካው ስንክሳር ከማደራጀቱ ከሰበካው፣
ከመተኮስ ከመዋጋት ከመማሩ ከማስተማር ከቅስቀሳው፣
ከማያልቀው የእግር መንገድ ከረሃቡ ከጥማቱ
ከስብሰባው ከቱማታው፣
ከድል ሕልሙ ከረጅሙ የትግል ሂደት ከተስፋ መቁረጥ
ከብዥታው።
ትግሉ ሁሉን በሸፈነበት፣
ትምህርት የራስ ሕይወት የዘመድ የጓደኛ ሕልውና
በተረሳበት፣
አካኪ ዘራፍ ማለት እንጂ ወደድኩሽ ወደድኩህ
በተገዘተበት።
ድንገት የገነፈለ ስሜት የፈነዳ የልብ ሲቃ፣
በትግል ጋቢ ያሸለበ እውነተኛ ፍቅር ሲነቃ።
ከጥይቱ ተኩስ የበለጠ፣
መዝሙሩን ሁሉ የዋጠ።
ከሁሉም በላይ የገነነ የሁሉን እንባ የቸረ፣
በትግል ለወደቀ ጓደኛ የተጻፈ ግጥም ነበረ።
“.......... ዛሬም አልተለያየንም ቃል ኪዳናችን
አልተጣሰም፣
ዛሬም አልተነጣጠልን ትዳራችንም አልፈረሰም።

4 መዝገብነሽ (ሂሩት) አንጋፋ ከነበሩት የኢሕፓ የቤት ታጋዮች አንዷ ከመሆኗም በላይ በውቅቱ ነሕ ይባል የነበረው መጽሔት ም/ አዘጋጅ ሆና አገልግላለች። ሴቶችን በማደራጀት ትልቅ ሚና የተጫወተች ሲሆን፥ የቀድሞው የኢሕአፓ አመራር አካል የነበረውና በደርግ ተይዞ የተገደለው የብርሃኑ እጅጉ ባለቤትም ነበረች። መዝገንነሽ ከሜዳ ትግል በኋላ በፍላደልፊያ በስደት ስትኖር ባልታወቀ ሰው በጩቤ ተወግታ ሕይወቷ አልፏል።



የእንግዳ ቤት ነው እንደ ድሮው ጎጆአችን አልቀዘቀዘ፣
ጣራውም አላፈሰሰ ቀለሙም አልደበዘዘ።
ውድ ጓድ አልደብቅህም ብቸኝነት ግን ይሰማኛል፣
መልክህን ማየት እጓጓለሁ ስምህን መጥራት ያምረኛል....”
መታገሉን እየታገለች በቆራጥነቱ ኮርታበት፣
መዘመሩን እየዘመረች መልኩን እያየችበት፣
ማስተማሩን እያስተማረች
እሱን ምሳሌ አድርጋበት፣
ለመሰዋት ተነሰታ
ሞትን ከባሏ አይታበት፣
ብስጭት ስትል ብቸኝነት ሲሰማት፣
እሱን ማጣቱ ሲያሳዝናት፣
ሞቱን መቀበል ሲከብዳት፣
ሳቅ ፈገግታው ሲታወሳት፣
መዝገብነሽ ብእሯን አነሳች
ሰቆቃዋ እንዲወጣላት።
አልሞትክም አለችው ሙት ባሏን፣
አልረሳሁህም አለችው ፍቅረኛዋን።
ፍቅር ከትግል በኋላ ተብሎ በተሰበከበት፣
መዋደድ ወንጀል በሆነበት፣
ዘመድ መናፈቅ በተኮነነበት፣
የሂሩት የፍቅር ትዝታ፥
የተዳፈነውን ኢጋየበት፣
ግማሹ አንገቱን ሰብሮ፥ እንባውን አነባበት፣
ያገለደመውን ኩሹክ፥ አፍንጫውን አበሰበት።
ያቺ ገጣሚ የት አለች? ብል በቀደም እለት፣
ሞታለች አሉኝ እንደዘበት።
አረፈች አሉኝ በአሜሪካ፣
በሳለ ጩቤ ተወግታ።

እንዳለችው ጓደኛዋን፥ እንባዋ ውስጥ አስቀምጣ፣
የራባትን ያክል ሳትበላ፥ እንደ ጥማቷ ሳትጠጣ።
ሞተች አሉኝ ከባሏ ተቀላቀለች፣
እንባዬ ውስጥ ተቀመጥ እንዳለች፣
ምን ይገርማል ለመሆኑ ድሮም እኮ የጎን ልጅ ነበረች።



# ምነው እማማ ጣርሽ በዛ?

በኮረዳ ውበት ተጠምዶ፥ቅስናውን እንዳፈሰሰ ቄስ፣
የቀጠሮ ሰዓት አልፎበት እንደተረታ ጠበቃ ገና ሳይከስ፣
ቤቱ አለማገር ተዋቅሮ ጣራው ሆኖ ካልጣለ አያፈስ።
በቅሎው ጠፍቶበት በምሽቱ ደብተራ ፈላጊ ለድግምት፣
ጅቡን ከመብል ሲገታ ዓይን አፍንጫውን ሲያግት።
ጠብመንጃው ነክሶበት ዱላ እንደሚፈልግ ወታደር፣
ሞፈሩ እንደ ተሰነጠቀ ማረሻው እንደ ተሰበረበት አርሶ
አደር፣
ምነው መና ሆነ? ምነው አላምር አለ ያንቺ ነገር?
ወረቀት ለምኖ ብእር እንዳጣ ተማሪ፣
ማሲንቆ ባንገቱ አንጠልጥሎ ጅማቱ እንደ ተበጠሰበት
አዝማሪ፣
ዛሬም ኖሮሽ ልታጭ እየበከንሽ ልትኖሪ?
ማኛውን ጤፍ ቸብችበሽ ዳጉሳ ለራት ልትጋግሪ።

ከእናትም እናት ሆነሽ  አሳድገሽ፣
እረሃብ ቸነፈሩን ችለሽ፣
የድህነት ወገብሽን ጠፍረሽ፣
ልኳኳል ላጊጥ ሳትይ የነበረሽን ሰጥተሽ፣
በደግነትሽ በፈሪሃ እግዚአብሔርነትሽ ታውቀሽ፣
ለክርስትና የበኩር ልጅሽን አስጠምቀሽ፣
በነሆሜር ተመርቀሽ፣
ከነሙሴ ጋር እንዳልተጋብተሽ፣
ዛሬ ምነው ማድያት ወረረሽ?
ምነው በመጠሪያሽ መንደፋደፍሽ፣

አዳራሽሽን ማፍረስሽ?
ልጆችሽም እንደ መርዳት ሊያሳምሙሽ?
እንደ መጦር ሊገፊትሩሽ?
ሳትሞች ሊናዘዙብሽ።
ምነው እማማ ኤሎሄሽ ስሚ አጣ?
ከዘራሽ ተሰባበረ ገበናሽ ከደጅ ተሰጣ።
ምነው የእኔ እናት ቀሚስሽ ተዘከዘከ፣
መቀነትሽ ተፈታ እግርሽም አፈከፈከ።
ኧረ እርገሚ ሳትሞች እንዳይገድሉሽ፣
የሰበሰብሽውን እንዳይበትኑ የገነባሽውን እንዳይንዱብሽ፣
ወሰኑን እንዳያስነኩ ድንበሽን እንዲያጥሩልሽ።
ምክርሽን እንዲሰሙ፣
እንዳቅማቸው እንዲያልሙ።
እርስ በእርስ እንዲዋደዱ፣
ከተቻለ  እንዲረዳዱ።
ለአንድነት እንዲጥሩ፣
ከስልጣን ማዶ ለሃገር ልማት እንዲሰሩ፣
በዛሬው ስራ ነገ  እንዳያፍሩ።
ሰው ያልፋል ሃገር ግን ያሳልፋል፣
የተጣላ  ሲከስር የተፋቀረ ያተርፋል፣
ብልህ የሆነ የዘራውን ያመርታል፣
ሰነፍ ገበሬ በቀጭ በተምች ይመታል።



# እስቲ በልማቱ እንጣላ

የዘመናት ትግል ስሌት የወጣት ሽማግሌ ደም፣
ከየት ተብሎ ሲተረክ፡- በማን ተብሎ ሲገመገም።
ሁሉም ድርሻውን ሲያሞጋግስ ያልተስማማውን
ሲያጥላል፤
ያለፈውን በትዝታ መጭውን በይሆናል እያሰላ፣
ይኸ ወንበር መጥፎ ነገር ከግራ ቀኝ ሰው አባላ።

እንደ ደጃ ሰላም ሰሞነኛ ባግዳሚ ወንበር ተጋደለ፣
ስሉስ የቀናው በጡንቻ ያልሆነለት ሽለላውን ቀጠለ።
ቆይ ግድ የለም ሆነ መሃላው፡
ባለፈ ጋቢ ተሸፋፍኖ መጭው ሁለ አስጠላው።
ቅኝቱንም አልቀየረ በነበረበት ቆሞ፡
ማንጎራጎር ብቻ ቀረው ብስጭቱን ተሸክሞ።

ኧረ እስቲ ዞር ብለን አይተን ማርጀታችንን እንቀበል፡
የጦርነት ከበሮ ይቅርና የሰላም ችግኝ እንትከል።
ቃታ ሳይሆን ማረሻ፣
ጦር ሳይሆን መዶሻ።።
እንጀራና አንባሻ ለተራበው፡ እንስጠው፣
ማቅና ዝተት እናልብሰው፣
በመሰለው ይቀናጅ በዘር ቋጠሮ አናፍነው።
እኔማ አማራነት አይገባኝ ኢትዮጵያዊነት ተዋህዶኝ፣
እንደ ባለሞያ ጥበብ የሕብረ ሕዝቡ ቀለም አስጊጦኝ።

የኦሮሞ አካል መሆኔ አኩርቶኝ፣
የትግራይ ታሪኬ አንጠራርቶኝ፣

የወሎ የእምነት ሃውልት አስደሰቶኝ፣
የባሌው ሸህ ሁሴን ናፍቆኝ፣
ሐረሬ ድሬ ውል ብሎኝ፣
ጎንደር ፋሲለደስ ታውሶኝ፣
የማርቆስ የባህርዳር ትዝታ ተብትቦኝ፣
የሰሜን ሸዋ እድገቴ ጋርዶኝ፣
የሲዳማ የወላይታ የጉጂ ሕብረ ቀለም አስደሰቶኝ፣
የጉራጌ ታታሪነት የዶርዜ ጥበብ አስቀንቶኝ፣
የወለጋ የቢል ሻንጉል ፈገግታ ታይቶኝ፣
ያርሲ ጉድሮ ያፋር ልበ ሙሉነት ተጠናውቶኝ፣
እንዴት ብዬ ልታጠር ኢትዮጵያነት ተላብሶኝ።

የዓለም ጭቁን ሕዝብ አንድ ነው ባልኩበት፣
ታጥፌ ጎጥ ቀበሌ አልልበት።

ሕዝብ ድንበር የለውም ብዬ ዛሬም በእምነቴ እጸናለሁ፣
የማይስማሙትን አከብሬ የራሴን ይዤ እሞታለሁ።
ለልማቱ ግን ልሰለፍ አቅም ጉልበቴ በቻለው፣
የእኔ ውስን ድኅማ አረሃብተኛውን ካቃመሰው፣
ድር ቢያብር እንዲሉ የጤና ችግሩን ከቀረፈው፣
የተሰበሰበ ተጠራቅሞ መሃይምነቱን ካስገፈፈው፣
መታገል ማለት መጨራረስ ነው የሚል ማን ነው?
ድህነት የሚጠፋ እንጂ አይደለም ቋሚ ነቀርሳ፣
ካመንበት ተሰባስበን አረሃብን ለማጥፋት እንነሳ።

ፈረንጆች ከመቀበል ይልቅ መስጠት ያስደስታል እያሉ፣
ለማን እንደ ለገሱ ስም ከመጥራት ይቆጠባሉ።
እናም ማን ተመሰገነ ማ፣
ሥራው ይጀመርና መንደር ቀበሌው ይልማ፣



በፖለቲካው እንፋጭ የትግል መስመር እናስላ፣
ወንድሞች በቅን ካሰብነው በልማቱስ እንጣላ፣
ለመታገለም ጤነኛ እንዲሆን ሳይሳቀቅ ጠግቦ ይብላ።
ለመልእክት እንዲያመች የተጻፈውን አንብቦ እንዲረዳ፣
ፊደል እንላክለት የተጣራ ውሃም ይቅዳ።
ወንድሞችና እህቶች ማን ይመስገን ማ፣
ምን መጥፎ ነገር ይኖርበታል መንደር ቀበሌው ቢለማ።

# የኪነቱ ንጉሥ

ልሳነ ጣዕመ ቃናውን ከዲያቆን ቅላፄ ወስዶ፣
አሰባበሩን ከወፍ ዜማ፥ እንጉርጉሮውን ከዱር እረኛ
አስገድዶ ፤
"ዋይ ዋይ" ብሎ፥እንደ አስለቃሽ ተለማምዶ።
እንደምትፈትል ሴት ወይዘሮ፥ ዓይነ ልቃቂት ጥሎ፣
እንደሚገላምጥ ጎረምሳ፥ ወደ ላይ ወደታች አንከባሎ፣
እንደ ሰራቂ የሰፈር ዳንዴ፥ ያየውን በጥቅሻ አስኮብልሎ።
የከረመ የወሊሶ አንበሳ፣
በዘፈኑ እጅ እንዳላስነሳ፣
ቀኑ ደርሶ ዘፈን አቆመ፥ መረዋ ድምፁ ሳሳ፣
ደከመው አሉኝ ገላው ዛለ፥ እግሩም ሳይቀር እጅ ነሳ።
ጥላሁን ያገር አድባር፥ የኪነት መደላድል፣
የማትችለውን አትጀምር፥ ያላሰብከውን አትከጅል፣
ያልሰራብህን ዝምታ አታምጣ፥ ጸጥ ብለህ ሰው
አትበድል።
ኧረ አሉ እንደ ጳውሎስ፥ ዘፈንህን ቀርቶ ለቅሶህን፣
ለመስማት የሚፈልጉ፥ ለማየት የሚጓጉ ዓይንህን።
አሉህ የግል ምርኮኞች፥ ዘመን የሚቆጥሩብህ፣
እንደ ሰገሌ እንደ አድዋ፥ እድሜ የሚያሰሉብህ።
ዜማህን ከጎደኛ ከፍቅረኛ ከቤተ ዘመድ፣
የሚያገናኙ ዓመታቱን ከቅላጼህ ድምጸ ሞገድ፣
ተነሳ እንጂ እንዴት በድንገት፥ ከመድረኩ ተገፍተህ
ትወርድ።
ጥላሁን የፍቅር ምርኮኛ፥ ጥላሁን የኪነት ምኩራብ፣
በዝምታህ ስንቱ ተንካ፥ በኩርፊያህ ምእመን ሊራብ?



የምትወድህ ምን አለችህ? የናፈቃትን ምን አልካት?
እንደ ተናደደ ደብተራ፥ ድምጽህን በዝምታ የቀጣሃት፣
ተስፋ እንደ ቆረጠ ወታደር፥ ቀኑን ያጨለምክባት፣
እንደ ተማረከ መኮንን፥ ዝምታን የተካንክባት፣
ኢትዮጵያን እንዳላሞገስክ፥ "ሃገሬ ሃገሬ" እንዳላልካት፣
መርገጥ ተሳነህ መሰለኝ፥ ከርሰ ማህጸኗን መረጥካት።
ያገሩን ሴቶች በመላ፥ "ሞናሊዛ" እንዳላልካቸው፣
ውበትን እንዳልፈለፈልክ፥ ፍቅርንም እንዳልፈለጥከው፣
ምሬትን እንዳላወጣህ፥ ቀረርቶን እንዳልሸለልከው፣
"ድምጻዊ ዘፋኝ ነኝ"፥ ብለህ ሞትን እንዳልቃኘኸው፣
ዛሬ ምን ተፈጠረ፥ ድምጽህን በድንገት ገደልከው፣
በአስፈሪ መቃብር ለስነህ፥ ኪነትን አብረህ ቀበርከው።
ጥላሁን አባክህ አትጨክን፥ ድምጽህ እንደሆን ምትክ
የላት፣
"እንከርዳድ" ብሎ ለማቀንቀን፥
"መለያየት ሞት ነው" እሚልባት ፤
የፍቅርን ቦታ አጠያይቆ፥ መውደድን የሚያሳምራት፣
ግዴ የለህም በኔ ይሁንብህ፥ ካንተ ሌላ ኪነት ሰው የላት፣
እያመመው የሚስቅ፥ ካልጋ ሆኖ የሚያዜምላት፣
ኪነት ካላንተ ማንም የላት፣
ይልቅስ አርካፉኔ በላት፣
አንተው አሳድገሃት፥ መልሰህ አንተው አትግደላት።
ቅርስ ነውና የውድ ሃገር፥ ከፍ አድርገን እናስቀምጣት፣
እንደ ጠዋት ፀሎት እንድገማት፣
አባክህ ቃልህን አትለጉማት፣
ቅላጼህን አትቅበራት፣
የኪነት ዓይንህን አታጨልም፥ እንዳኮራችን እንኩራባት፣
ጥላሁን ቃልህን አትግደላት........

# ካንቺ ከመጣ ኤርትራ!!!

በኢትዮጵያን ሪቪው APRIL 1993 እትምት ላይ የወጣ

ሳልከድሽ አንቺ ከካድሽኝ፣ ሳልርቅሽ አንቺ ከራቅሽኝ፣
መውለዴን ከተጠራጠርሽ፡- ጉዲፈቻ ነበርኩ ካልሽኝ፤
በመጠሪያዬ ካኮረፍሽ መለየቱን ከወደድሽው፣
ባሕሌ ዛሬ ካስጠላሽ ብቸኝነትን ከመረጥሽው፣
ድሃ እናት ከሆንኩብሽ ከቤት መውጣት ከሆነ ምርጫሽ፣
ኤርትራ ዕድልሽ ይስመር ካሻሽበት በወግ ያግባሽ።
አብረን ካልተጣጣምን ንትርክ ከሆነ ኑሯችን፣
የውጭ ምስክር ከተጠራ አንድ አካል ለመሆናችን፣
ይቅር ከእንግዲህ መናቆሩ ጥቅም የለውም ለሁላችን።
መዳማት ይብቃ ዳግመኛ ያለፈውስ ለማን በጀ፣
ሕፃን በውጊያ መሃል ተወልዶ በውጊያ  መሃል ካረጀ።
መጫወቻው ጥይት ከሆነ ትዝታው ጦርነት ብቻ፣
ተውት በሰላም ይሥራ ቤቱን ትዳር ይመስርት ጉልቻ።
ልጆቹ ግን ከጮሁ፣ እያቴን ብለው ካስቸገሩሽ፣
ኑሮም እየከበደ ድንገት ችግር ከበዛብሽ፣
መለየት መጥፎ ነውና የዘመድ ናፍቆት ከጠናብሽ፣
ቤቴ መቼም ክፍት ነው አትፍሪ ይልመድብሽ።



# [5]ደብረ ብርሃን

ደብረ ብርሃን የጥንት መንደር፣
ደብረ ብርሃን የብርድ ሰፈር፣
ደብረ ብርሃን የጎበዝ የጀግና ድንበር።
በኃይለ ማርያም ማሞ የጦር ሜዳ፣
የዘራይቆብ ፍርድ ሲቀዳ፣
መናፍቅ የተደበቁብሽ ወደ ጓዳ።
ኃይለመለኮትን አሳድገሽ፣
ምኒልህን አንጎለላ ላይ ወልደሽ፣
ቀረሽ አሉኝ የወላድ መካን ሆነሽ።

ደብረ ብርሃን የብርሃን ጮራ፣
እምነቷን አጠንክራ፣
መልኳን በግማደ መስቀል አሳምራ፣
ሳታረጅ አረጀች አሉኝ፥
አዲስ ቁም ነገር ሳትሠራ፣
ቆዳዋ ሳይሸበሸብ፥
ፊቷ ላይ ማድያት አደራ።
ደብረ ብርሃን፣
የአገር ብርሃን።
የአርበኞች መሸፈቻ፣
የጦስኝ በግ መሸመቻ።
የአንኮበር ማለፊያ በር፣
የመንዝ የይፋት ማግና ድር።

---

5 አሁንም ዳግም አገሬ ገብቼ ደብረ ብርሃን ጎራ ብዬ  የገጠምኩት ግጥም።

የተጉለት የቡልጋ ገበያ፣
የጅሩዎች መተያያ።
የስላሴን ጣራ ኮርኒሷን በሰዓሊዎች አስደምቃ፣
መምህር የቆሎ ተማሪ በቀሚሷ ስር ደብቃ፣
ታፍና ትኖራለች በለቅሶ ሲቃ ታምቃ፣
የድሮ ውበት ቁንጅናዋን በአዲስ መጤዎች ተነጥቃ።
ደብረ ብርሃን ያላረጀች፣
የጥንት ጦረኞችን ያማለደች፣
አልሰምር ሲል ሰገሌን የወለደች፣
ጣልያንን ያንበረከከች፣
መገዛትን ማጎብደድን ያለመደች፣
እነ ሸዋረገድ ገድሌን እንዳልወለደች፣
ዛሬ ያለ ጧሪ መና ቀረች፣
ትንሳኤ  የግድ እንዲሉ፥ ጊዜዋን ጠብቃ ትነሳለች።



# ለእርሱ ብርታት ለእኔ ጽናት

ከደከምኩብህ አበራታኝ፣
ከተደናቀፍኩ ሳልወድቅ አንሳኝ።
ሰብእ ነኝና ድኩም ፍጥረት፡
ወድቄ  እንዳልቀር እንደ ኩበት፤
ምርኩዝ ሁነኝ ጠባቂ፣
እረዳት ሁነኝ ጠያቂ።
ለጠሉኝ ልብ ስጣቸው፣
ብርታቱን አትንፈጋቸው።
እኔ ባሪያህማ  ደካማ ነኝ፣
ለመጽናናቱ ጉልበት ስጠኝ።
ለእኔ እንደሞትከ ለሃጥያቴ፣
ይቅር እንዳልከኝ ከድከመቴ፤
አበራታኝ ይቅር ልበላቸው ካንጀቴ።
እኔን አንደ ወደድከኝ፣
እንድወዳቸው ጽናቱን ስጠኝ።
ቸር ነህና ይቅር ባይ፣
የማያልቀው ምሕረትህ ይታይ።
ቢበትኑ ስብስቡን፣
በዘር በጎሳ ቢለዩን፣
በፖለቲካ  ቢያበራዩን።
አምባ ገነንም ቢሆኑ፣
ምሕረት ስጣቸው ይዳኑ።
የሳት አለንጋ ሳይገርፋቸው፣
ሰይጣን ሳያቀሳቸው፣
ዲያብሎስ ሳይሰርጋቸው፣
የክህደት ማቅ ሳይወርሳቸው፣

አባከህ ፈጣሪ መልሳቸው፣
የፍቅርን መንገድ አሳያቸው፣
ግፍ በዛ አሁንስ ይብቃ  በላቸው።
ለእኔም ብርታቱን አትንፈገኝ፣
ከውዳሴ ፖለቲካ አድነኝ፣
በይቅርታህ ጀቡነኝ፣
ሰይፉን ሳይሆን ፍቅሩን ስጠኝ፣
እንደ ሰብአ ሰገል የብርሃን ጮራ አሳየኝ፡
በጥንካሬ እንጂ በድከመቱ አትዳኘኝ።



# [6]የዘሩ ኽሸን ስንብት

ማሰሮው አይገነፍልም መከላሊቱ ተከደነ፣
ከእንግዲህ ቁሌቱ አይሸትም ምድጃው ተዳፈነ።
ኩፍ አይልም ሊጡ በጭራሽ እርሾ ሳይደባለቅ፣
አፍለኛ ይሆን እንደሁ እንጂ ለይድረስ የሚሰነቅ።

ጠላ ምን ጠላ ሆነ ብቅል ጌሾ ካልገባበት፣
ቀሪቦ ይሆን እንጂ ጥማት የሚያረኩበት።
ምን መታረቅ አለ ሽማግሌ ያላየው ጥል፣
ዛፉ ተገነዳድሶ አራሙቻው ሲበቅል።
ታሪክ እራሱን ፈጠረ ታሪክ እራሱን ከዳ፣
ያልነበረ ካደባባይ ታዋቂውን ወደ ጓዳ።

የሚሳሳት የሚሠራ ነው ይሉ የለ ምሑሮቹ፣
የሰሩት ተበታተኑ ያልሰሩት ተመቻቹ።
የነበሩት ከሰሙ ያልነበሩት ሕይወት ዘሩ፣
ዓየር ባየሮች ከበሩ ነጋዴዎቹ ከሰሩ።

እንዳሰበው ባይሆንም ቅሉ እንደ ጅምሩም ባያምር፣
የተማሪው ስብስብ ቅንጅቱ ባይሰምር፤
የረገፈው ሁሉ ወጣት አርማው ወደ ላይ ባይሰቀል፣
እንደ ታደሉት ባይሆንም ሐውልት በስሙ ባይተከል።

ታሪክ ሠርቷል አሌ አይሉ የተኛውን ማንቃቱን፣

---

[6] የቀድሞ የኢሕአፓ መሪ የነበረው ዘሩ ክሸን በሞት ሲለይ የጻፍኩት የመሰናበቻ ግጥም።

አይወድቅም ያሉትን መጣሉን፣
አይሞትም ያሉትን መገርሰሱን፣
አሌ አይሉም መታገሉን፣
እየሞተ ማንሰራራቱን፣
አሌ አይሉም እየዳኸ መራመዱን፣
ሲዳከም መሽመድመዱን፣
አሌ አይሉም አዲስ ምእራፍ መከፈቱን፣
የትግል ተመክሮ ማካበቱን፣
አሌ አይሉም ዛሬ የወደቀው ዛፍ፣
የትናንት ዋርካ መሆኑን!!!



# ሚሊኒየም

*ነሐሴ ፭ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም*

የቀን ከምር የድሜ ሙላት፣
ጀንበር ወጥቶ ጀንበር መግባት፣
ክረምት መጥቶ በጋ መርሳት፣
ጸደይ አይቶ ጮቤ መምታት።
ተደምሮ ጨለማ ብርሃን፣
ተቀምጠን ሳንነሳ ሚሊኒየም ይኸው ሞላን።

የሥልጣኔ የእውቀት መንደር፣
የነሉሲ የሳባ አገር፣
ያሳዝናል በነበረበት ቆሞ ሲቀር።
የታሪክ ቅርስ የአከሱም ሐውልት፣
የጎንደሩ ቤተ መንግሥት፣
የላሊበላው የእምነት ቅስት፣
ለነበረ መረጃ እንጂ፣
መቸ ሆነ ተስፋ ላገር ልጅ።

የጅማ ታሪክ የሐረር ግንቡ፣
የተወራለት ጥጋቡ፣
የታለ ዛሬ ጠፍቶ፣
ባፈ ታሪክ ብቻ ተሞልቶ።
የተጠመቅነው ከሰው በፊት፣
አልተቋቋምንም እንጂ የእምነት ግፊት።
ሙስሊሞቹን እንዳላስጠጋን፣
እኛን ዛሬ ስደቱ ጎዳን፣

የሰው ፊት ግርፊያ መከራው እያላጋን።
ለአፍሪካ አንድነት እንዳልታገልን፣
ለዓለም ሰላም እንዳልተጋን፣
ተለያየን ሰላም ነሳን፣
የማይታጨድ ዘር ዘራን፣
ዛር ውቃቢው አስጎራን።
ከውጭ ጠላት ተፈላልመን፣
ወራሪውን አሳፍረን፣
በስልጣን ተቆራቁሰን፣
የጎበዝ አለቃ  ተክለን፣
በፊውዳል ሥርዓት ታምቀን፣
በዘውድ እምነት ተሸብበን፣
በዘመን ድምር ሚሊኒየም እንላለን።
ከድርቡሽ መተማ መሬት፣
ከግራኝ ደጋ ቁልቁለት፣
ከጣልያን አድዋ አቀበት፣
የስንት ጀግና ደም ፈሰሰበት፣
አንገት እንደ ጥንግ ተለጋበት።

ታሪክን እንዳልሰራን፣
ለጥቁር ተስፋ  እንዳላበራን፣
ዛሬ በረሃብ አንጀት፥
ይኸው ሚሊኒየም ሞላን።

በውጭ መድኀኒት ስንፈወስ፣
በመጤ ጳጳስ ስንቀደስ፣
በእርጥባን ስንደገስ፤
ተከማምሮ ችግራችን፣
ዓመት ተዋልዶ  በላያችን፣



በመኃይምነት ቋጠሮ፣
ሚሊኒየም ሞላን ዘንድሮ።

የውጭ  እምነት ተከትለን፣
መጤ ሃሳብ መርህ ብለን፣
ስብስቡን እረሽነን፣
ከጉያችን ፋሽስት ወልደን፣
በመንደር በቀየ ተለያይተን፣
በዘር በጎሳ ተከፋፍለን፣
አይቀርምና ዘመን ቆጥሮ፣
ሚሊኒየም ሞላን  ዘንድሮ።

ትግሉም እየፈረሰ፣
ድንቁርናው እየነገሠ፣
ጉራማይሌ እንዳልተነቀሰን፣
በአጉል መፋቂያ ታበስን፤
ጥርሳችን ተሰባበሮ ፍንጭት ሠራ፣
በላዩ ላይ ልጋግ ደራ።
የዓመት ክምር ተቆጠረ፣
ሕብረታችን አልሰመረ።

እይታችን ጥላ አለበት፣
መጭውን ግን እንሥራበት፣
መለያየትን እንተውበት፣
መቻቻልን እንልመድበት፣
ባዶ ዘመን እንደምርበት።

# አሲምባ

ተራራ አይደልም ጉብታ እርቅናን የቆመች የድንጋይ ቋት፣
አውሬው ጥሏት የጠፋ አሞራ ወፍ የመሸገባት፣
እንደ ቀበሮ ዝንጀሮ ፍየል የሚያድንባት፣
በለሰ የሰፈረባት ሐምሊ የነገሰባት።
አሲምባ የትግል መንደር፣
አሲምባ የሸሸት ሰፈር።
አሲምባ፣
የወጣት ታጋይ አምባ።
ጉያሽ በፈንጂ ሲናድ ትከሻሽ በነፋሪት ሲደበደብ፣
በገበላሽ በሽተኛ ሲያገግም ጥይት
ፈንጂው ሲቀረቀብ።
አሲምባ ፣
የወጣት ታጋይ አምባ።
አሲምባ  የስደት ጎጆ አሲምባ የቅርቃር ሰፈር፣
ምን አልሽ ዛሬ? ዘር ውልደትሽ
ሲተረተር?
ኢትዮጵያዊነትሽ ሲያከራክር
እትብትሽ ከማዶ ሊቀበር ሲሞከር።
እኮ ምን አልሽ? ቀላድ ሊጥሉብሽ ሲያስቡ፣
ችካል ሊተክሉብሽ ሲያደቡ።
አሲምባ የአሊተና ቤት የሰንገደ የከለአሳ፣
ትናንት ታጋዩ እንዳልዘመረ በጉያሽ እንዳላገሳ፣
ጠላትሽ እንዳልፈራ እንዳልባነነ ስምሽ ሲነሳ፣
መሰደድ ሲያራቁትሽ ማንም ሊደፍርሽ ተነሳ።
የነደረጀ  የነፍስሐ የነኤልያስ የነይርጋ፣
አጽማቸው ሳይሰበሰብ የታሪክ ምእራፉ ሳይዘጋ።



አርባ  ሰማንያ መንፈቅ ሙት ዓመታቸው ሳይደገስ፣
ለእነ ጌትነት ሳይረገድ ለነ ጉርሙ ሳይለቀስ፣
የተቀበረው ቦምብ ሳይቆፈር ባሩድ ቀለሁ ሳይመለስ፣
ዶሴው ሳይሰበሰብ የትግል ስንክሳር ሳይከለስ።
አሲንባ  ያአፋር ምላሽ አሲምባ የአጋሜ  ድንበር፣
የዛለ አንበሳ ጥላ አሲምባ የሳሆ መንደር፣
አሲምባ የወጣት መከታ አሲምባ  የኩርፎ ሰፈር።
የነደበሳይ ቀየ የነስባጋዲስ ሜዳ፣
ዛሬ ፈታኝ መጣባት ልጆቿን ሁሉ አሰድዳ፣
ከተማ የገቡትን ከፎቅ እናት አስወርዳ።
አሲምባ የትግል ቀራንዮ አሲምባ የሰሜን መንታ፣
አልሞተችም አለች አሉኝ ደረቷን ለፀሐይ ሰጥታ፣
ሳትፈልግ በግዳጅ በነመነኩሲየቶ ታጭታ።
አትጨፍሩልኝ ብላ ተማጽና እስከ እሚያልፍ እንገቷን
ደፍታ።

አሲምባ
የታጋይ ወጣት አምባ።

# [7]ሕጻንም ለካ ይሞታል

የማይታመን ሆነብኝ ምኑን ከምን ልናገር።
ንጋቱ ገና ሳይጀምር ጭለማ መንደሩን ሲያለብሰው፣
እድገቱ ተወርቶ ሳያልቅ እልፈቱ አገሩን ሲያዳርሰው፣
አሃዱ አብ ለማለት ቸኩሎ አሜን ከፊቱ ሲጠልፈው፣
መልስ የሌለው ጥያቄ ፍች የሌለው እንቆቅልሽ ነገር፣
ተንስኡ ለማለት አሰቦ በሰላም ወደቤት ግቡ ሲያሰኘው።
እኮ ምኑን ይገፍ ልንገራችሁ ለወሬ የማይመች መርዶ፣
ወጣቱ ማቲው ዘመቻ ከጓደኞቹ ጋር ከራንች ወርዶ፣
የ ፲፪ ዓመት እድሜ ተመክሮውን ይዞ፣
እሱም እንደ ወላጆቹ የገጠር መንገድ ተጉዞ፣
በለመደበት ዝምታ በትህትና ታጥቆ፣
እንደ ሜዳ ተጋዳይ የቀን ስንቁን ሰንቆ፣
ካሰልችው ከተማ ወጥቶ፥ ከዛፍ ሥር አረፍ ብሎ፣
ቀረ ብዬ በንፋስ ግፊት፥ በወደቀ ዛፍ ተታሎ?
እኮ ምን ልንገራችሁ? ባውሎ ንፋስ መሃል ማለፉን?
በዛፍ ምት መረታቱን?ለመዝሙር መጋበዙን?
በሰረገላ መጓዙን?
ምን ልበላችሁ ወንድሞቼ?
ተወለደ ሲባል መሞቱን?
ምን የምስራች አለና፥ የያዘው ጧፍ መጥፋቱን?
ጎል አላገባም እኮ ዛሬ፥ ከሳጥን መከተቱን?

7 የ ፲፪ ዓመት እድሜ የነበረው ናቲ ብርሃኑ ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ለሽርሽር ሄዶ የደረቀ ዛፍ በንፋስ ግፊት ወድቆበት መሞቱ ልቤን ስለነካው ባጭር ለተቀጨው ወጣት መሰናበቻ የጻፍኩት ግጥም።



ሊዘምርልን አልመጣም እኮ፥ ከመልአክት ዜማ
መቀናጀቱን?
እኮ ምኑን ልንገራችሁ? የማያምናት እናቱን መከዳቱን?
ወንድሞቼ ምን ላውራችሁ? ካባቱ ፊት ድንገት
መጥፋቱን?
እድርጎት የማያውቀውን፥ ከህቶቹ መደበቁን?
የቱን ነው የምትሉኝ? ከቤተክርስቲያን መጥፋቱን?
ሳይስቅ ፊቱን ማጨለሙን፣
ገና ሳይሮጥ መድከሙን፣
ሳይበላ መበላቱን?
ሳይጠጣ መቀጨቱን?
ሕጻንም እንደ አዋቂ፥ ሳይታሰብ መሞቱን።
እኮ የቱን?
አምላክ ሆይ አገልጋይነቱን ከወደድከው፣
ሕጻኑን ለዝማሬ ከመረጥከው፣
አትከልክሉ ብለሃልና፥ መች አስቆምን ከጠራኸው።
አንተን መስማት ከመረጠ ውሎ አደረ፣
ሌት ከቀን እንደዘመረ፣
ይቺንም እድሜውን ጨረሳት፥ አንተን እንዳከበረ።
እሱንስ በቤቱ አስቀመጥከው ሳይመሽ ጸሎቱን ሰምተህ፣
እሱንስ መርጠህ አቀፍከ፥ ከልጆች መሃል አይተህ።
ተአምርህ ብዙ ነውና፥ ቤተሰቦቹን አስባቸው፣
በፈውስ እጅህ ደባብሰህ፥ የጽናት በትር ስጣቸው
ጌታ ሆይ ጓደኞቹን አትርሳ፥ አንተ ብርታት ሁናቸው።
የተጎዳነው ሁላችንም ነን፥
አንተ አይዞአችሁ በለን፣
አገልጋይህን ወስደሃል እኛንም ለንስሐ ሞት አድለን።
ማቲው ደህና ሰንብት፥ የልጅ አዋቂ ሆንክብን፣
ከናትህ ይልቅ፥ አማላጁን መረጥክብን፣

አባቴ ፈጣሪዬ ነው ብለህ፥ ሳናስበው ተሰወርክብን።
እህቶቼ ጓደኞቼ፥  ጻድቃኖቹ ናቸው አልከን፤
አንተ በዘለዓም ደስታ፥ ታጅበህ እኛን ለሐዘን ጣልከን።
እናም አምላክ ሆይ ልጅህን ተረከብ፥ ለኛም ብርታቱን
ስጠን፡
በመንፈስ ጥላህ ሥር አድርገህ፥ መጽናናቱን አትንፈገን።

አሜን አሜን



# እማማ

2/4/1976
ሔልከሬ ባሴ

የእናት እጅሽ ናፍቆኛል እራሴ ይዘሽ ደባብሽኝ፣
ቁጣሽ አሁንም ይታየኛል ሳቅ ኮስተር ብለሽ ገላምጭኝ፣
አሁንም አልጠገብኩም ጥርግራጊውን አጉርሽኝ፣
ያንቺ እጅ ይጥመኛል ከቁሌቱም አቀማምሽኝ።
በአከፋይ አንጀትሽ ደፋ ቀና ስትይ አየሁ፣
"አይ ፋሲካ ልጄ ሳይኖር" ስትይ ሰማሁ፣
እንዳምናው የለሁ ዛሬ ብዙ እርቄ ሄጃለሁ፣
ዶሮም አላረድኩልሽ ዘንድሮ፥ ያለፈውን አልማለሁ።
....ስሜን ጠርተሽ
"ና ቶሎ በግዜ  እረድልኝ" ስትይኝ፣
"መቼም ትጠማለህ አይደል?" እንዳልከፋ ሳቅ ብለሽ
ጠይቀሽኝ።

.... ጋቢው ተሠርቶ  አለቀ?
የሽማኔውን ከፈልሽው?
ካሎስ ነው ባለ ጥለት ለመሆኑ ምን አረግሽው?
የመቀነትሽ ጥለት ሽብሽብ ቀሚስሽ ይታየኛል፣
ዛሬም እንደ ልጅነት ጭንሽ መሃል መደበቅ ያሰኘኛል።
ካለሁበት ፋሲካን ዳግም የኋሊት ስመለከት፣
ትዝ አለኝ የካች አምናው ያወጋሽኝ  በለሊት።

ልጄ  ብለሽ

ጠላት መጥቶ የሞሶሎኒ ሰላቶ፣
ጀሌ በአጋዴን ድንበር ጥሶ፣
ከተተ ተብሎ ሁሉም ጦር ሰብቆ ለምዱን ለብሶ።
ኢሚን ኤልከሬን ጨረቲን፥
በእግር ጉዞ አቋርጠን፣
የጥምቀት ለት ከሰላቶው፥
ጭል ባለው በረሃ ተጋጥመን።
እንደ ወጉ በቀያችን ማርያም ከሜዳ አድራ፥
ሚካኤል አብሯት ተዳብሎ፣
ለጥምቀት አዲስ ተለብሶ ሆያ ሆዬ ተብሎ ።
ሆታ የነደብተራ ዝማሬ የሴቶች ውጣ ውረድ እስክስታ፣
የሰለት ጭፈራ ቅደም ተከተል ተርታ።

ቀርቶ

ጠላት መድፉን እንደ ደብተራ ሲያስቀድስ፣
መትረየስ እንደ ጥንግ ከግራ ቀኝ ሲተራመስ፣
ጦር እስክስ ሲል የማርያም ስለት የዓመት ያድርስ፣
የሚጠጣው ጽዋ ሳይሆን የደም ቅጅ ጥንስስ፣
የሚበላው ዳቦ ሳይሆን የአሸዋ አፈር ድግስ።
ብለሽ ያወራሽነ ታወሰኝ፣
እኔም እንዳንቺ ወግ ደረሰኝ።
የጠመቅሽውን ጠላ ጽዋ በኮዳ ውሃዬ ቀምሼ፣
በዳቦ ፋንታ ደረቅ ቁሽቋሽ ደቁሼ።
አወይ ፋሲካ ብዬ ፋሲካን አከብሬአለሁ፣
ዓመት በዓሉን በበረሃ በቆንጥር ሥር አክብሬአለሁ፣
እንደ አምናው አብሬሽ ሳይሆን ብቻዬን በጥበቃ
ገድፌአለሁ።
ያ ያንቺ እኔን ለማየት መጓጓት፣



ትምሕርት ቤት ተዘግቶ ብሎ መመኘት።
ዛሬስ አልሰመረም እማማ፣
ቤቴ ጫካው ዱር ሰው የሌለበት ባድማ።
ዘመዴ ቆንጥር አሸዋ አብሮኝ ያለው ብረት ሳንጃው፣
ፋሲካየም ሰው መግደል በአስከሬኑ መጫወት ነው።
ከዚህ ፋሲካም አያውቁ ዓመት በዓልም የላቸው፣
በመቆየት ሰልችተዋል ዘመድም አይናፍቃቸው፣
ጭዳም እንረድ አይሉ ደም መመልከት ሰልችቷቸው።
ይቅር እማዬ ብዙ ነው ጭንቀትና ብሶቴ፣
በበረሃ በሩቅ አገር ስደቴ።
የሠራሽውን ምግብ የደገስሽውን ድግስ፣
ጎረቤት ተሰብስቦ እንደ እኔ ሆኖ ይቃመስ።
ያከፋይ አላመጣሁም እማማ ዳቦም የማስጋግርበት የለኝ፣
ሽቶም አልገዛሁ ሱቅ የለም ጭል ባለው በረሃ ነኝ።
ብቻ እድልሽ ተቃንቶ እኔን ማየት ካበቃሽ፣
ቃል ልግባ በመጣሁ ጊዜ ላጫውትሽ፣
ባጋጠመኝ ፋሲካ ሌሊት ተነስቼ ላጋድፍሽ።

# [8]ትእግስቱን አድለን

02/03/2007

ቃል ነበርና በፊት ቃልም ሕይወት እንደሆነ፣
የነገሡ ድቅድቅ ጨለማ በብርሃን እንደ በነነ።
አየር እሳት መሬት ውሃው ሕይወት እንደ ፈጠረ፣
ያልነበረ ተወልዶ ሸር ተንኮል እንደ ጀመረ፣
ማቆም እኮ ትችል ነበር ትእዛዝህ እንደ ከበረ።
የምልአተ መሬት ሕግን ደንብህ ገና ሥራ ላይ ሳይውል፣
ያረገውን እየካደ ለሐሰት በስምህ ሳይምል፣
የሃጥእ ልቡ ሳይነድ የተንኮል ገፁ ሳይፍም ሳይግል፣
መወሰን ትችል ነበር የውንብድና ጨቤ ሳይስል።
ስምህን መከታ አድርጎ በቃልህ ሳይጠለል፣
በፃድቃን በቅዱሳን መሬት እንደ እንክርዳድ ሳይተከል፣
የይቅርታ ፈውስህን ሳይክድ በቂም በቀል ሳይታጀል፣
በቃ ለምን አላልከውም በቀሪ ንብረት ሳይደለል።
ስማን ጌታችን መሃሪ ነህ አሁንም አትራቅ ይቅር በለን፣
መናቆር ማፋጀቱን ግፈፍልን ፍቅር ትእግስቱን አድለን፣
ሞትን ላንተ ቤት መንገድ እንጂ በቁም ሳንሞት
አትግደለን፣
መዋደድን አዝንብልን መከባበር መቻቻልን መግበን፣
ግለኝነትን አሽቀንጥረህ በሕገ ቃልህ አስጠልለን።
መሃረነ ጌታችን ከዘር ከጎሳ መዓት አውጣን፣
በሰብእ እምነት አጥምቀን፣

[8] በዳላስ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አካባቢ የተፈጠረውን አለመግባባት መንስኤ በማድረግ የተጻፈ ግጥም።



ከሥጋ ወንድም አታቆራኘን፥
ከመንፈስ ወንድም ጋር ደባልቀን።
አይሳንህምና አንተ ዳግም ትእግስቱን ስጠን፣
እንደ ሥራችን ሳይሆን በምሕረትህ አስበን።





ዳግማዊ ተኮላ መኮንን
Dagmawi T. Mekonen

ብስራት ተኮላ መኮንን
Bisrat T. Mekonen





አብይ ተኮላ መኮንን
Abiye Tekola Mekonen
Mekonen

ሩት ተኮላ መኮንን
Rute Tekola





ከቀኝ ወደ ግራ ባለቤቴ ማርታ፣ እህቴ ደብሪቱ በሕይወት የሌለው ወንድሜ መስፍን መኮንን ዳግማዊ እኔና ብስራት።



ውድ ባለቤቴ ወይዘሮ ማርታ አሰፋ

# ጓደኛነትሽን ላመስግን

ካገር ለቅቄ  በልጅነት መጥፎው ደጉ ሳይገባኝ፣
ትግል እንደ ግዴታ ተጭኖ ገጠር ለገጠር ሲያለፋኝ፣
የጓደኞቼን ሞት እያየሁ ሐዘን ግራ ቀኝ ሲያዳፋኝ።
እምባም ያልሰራበትን ከዓይኔ  ከቋቱ ሲጠፋ፣
ያለቀሰው ወደ ላይ ሲፈነጠር፥ የጨከነው ከሚዛኑ ላይ
ሲያደፋ፣
ስንት ነገር አለፈ ስንት ችግር ተገፋ።
አብረን ከወጣን ጓደኞቼ ተያይዘን ልንመለስ፥
ቃል አስቀድመን  እንዳልገባን፣
ከሕዝቡ ጋር ሰልፍ ልንቆም እንዳልማልን፥
መራሩ ሞት አከዳዳን።
የወደቁ ተቀበሩ መርዶ ለዘመድ ሳይነገር፣
አሉ እኮ እያለ ወላጅ ባሕር ማዶ ከዳር አገር።
ታዲያ ያን ሁሉ አልፌ የስደት ኑሮ ስጀምር፣



የሆነውን ሳሰላስል ስቀንስና  ስደምር።
የተዋጣ ዐብይ ነገር፥
ያተረፍኩት ብሥራት በሕይወት ዘመን፣
አንቺን በማግኘቴ ብቻ ነው፥ መፅናኛ ላለፈ ሐዘን።
አንቺ ነሽ ወሬዬ እሚጥምሽ፥
ጠፋህ እኮ ብለሽ የምትፈልጊኝ፣
በስሜ ስለት የገባሽ በጸሎት የማትረሽኝ፣
አመመህ ብለሽ የምትሰጊ ግንባሬን የምታሻሽኝ።
አንቺ ነሽ የቆይታ ትርፍ፥
ትእግስተኛ የሩት እናት፣
መጥፎ  መናገር የማታውቂ፥
የቀልድ ቁም ነገር ባላባት፣
ባንቺ ሰላም ከቤት ባይኖር፥
እንደ እኔ ትእግስት አልባነት፣
ድሮ ገላግሎኝ ዛሬ አፈር ነበርኩ፥
የማይቀረው ጥልመተ ሞት።
አሁንማ አፍርቼ  ላንቺ መቀጫ እኔን ሰጥቶ፣
ለእኔ  ደስታ  አንቺን አምጥቶ፣
በተአምሩ ያኖረኛል ቤቴን በልጅ በሳቅ ሞልቶ።
የውጭ  ብስጭቴን ጥዬ በሩን ስከፍት እንድረሳ፣
ልጆቼን አሰልፎልኝ በብቸኝነት አልከሳ።
አሁንማ የልጆች አባት ባለጓዝ የድሮ አርበኛ፣
ባለፈ  እየተከፋ ባገኘው ተደስቶ የሚተኛ፣
መተኮስ የረሳ አዳኝ  መጓዝ ያቆመ መንገደኛ።
እኔን ደካማውን ለወደድሽ፥
ላልተረታሽ ባሉባልታ በችግር፣
ላንቺ መንፈሰ ጽኑነት ጥንካሬሽንም ልመስክር፣
ለደግነትሽ ደጅ ልጥና ለእናትነትሽ ተንበርክኬ፥
የቀናውን አንገቴን ላቀርቅር።

# [9]ደህና ሰንብት አበጀ

11/10/2000

ተፈጥሮም የራሱን ሂደት እድግቱን እየጠበቀ፣
ያልታሰበ እየፈጠረ ገና በጉዞ ላይ፥
ያለውን በድንገት እየነጠቀ።
ያልተጠራበት እየገባ፥ የማያውቀውን ቤት እየከፈተ፣
ዛሬ ገና ድል መታ ጀግናውን ይዞ ተካተተ።
ምንድ ነው ሞት? ወንድሞች፥ መተንፈስ ማቆም
ሕይወት ማጣት!!
ከመሃል ጠፍቶ መቅረት?
መሰወር ለዘለዓለም መረሳሳት?
እንዲያ ከሆነስ አልሰመረም፣ በጭራሽ ግቡን
አልመታም ።
እጁን ቢይዘው ብቻውን አግኝቶት ከመንገድ ላይ፣
ስሙንስ አይቀብረውም ታሪኩ ሕያው ነው ከሞት
በላይ።
እናም አንቀበልም ሞትህን፥ የሞተስ ታሪክ ያልሠራ፣
እኛ አናወራም መቀበርህን የሚቀበር በተግባሩ
የማይኮራ።
በምግባሩ የማይተማመን ባደረገው ሁሉ የሚያፍር፣
በተናገረው የሚጸጸት አንገቱን የሚያቀረቅር፣

9 የአየር ወለድ አዛዥ የነበረው ኮሎኔል አለማየሁ አስፋው የደርግን ፋሽስታዊ አገዛዝ በመቃወም ለትግል ወደ ኢሕአፓ ተቀላቅሎ የሰራዊቱ ምክትል መሪ በመሆን ያገለገለ ቆራጥና እኩሪ ወንድም ነበር። የሰራራዊቱ አመራር አካል ሆኖ ፓርቲው አንጃ ናቸው ያላቸውን ተጋዳዮች በሞት ይቀጡ ሲባል የተቃውሞ ድምጽ በመስጠቱ የሚመሰገን ጀግና ነው። የትግል ስሙ (አበጀ) የነበረው ኮሌኔል አለማየሁ አስፋው በዋሽንግተን ዲሲ በስደት ላይ እያለ በድንገተኛ ህመም በሞት ተለይቷል።



ያንተ የሚያኮራ ነው አበጀ፥
በሕይወት ሳለህ ሳንናገር በሞትህ ሳልስት
እንመስክር።
ለሕዝብ መቆምን መርጠህ የግል ጥቅምህን
አሽቀንጥረህ፣
ከላብ አደሩ አብረህ ከአርሶ አደሩ ተቀላቅለህ፣
እንደ ሌላው ሳትመጻደቅ እንዲህ እኮ ነበርኩ ብለህ፣
ከዓላማህ ሳትዋዥቅ በእምነትህ ሳትደራደር፣
ባልመሰለህ ፍርድ ላይ ባለመስማማትህ ሳታፍር።
ምነው? ዛሬ ታዲያ ጓድ አበጀ ገና ድፍርሱ
ሳይጠራ፣
የተንከራተትክበት ሜዳ አቀበት አንተን መሰል
ሳያፈራ።
ወገብህ ገና ሳይጠና መንገድ የጎዳው እግርህ
ሳያገግም፣
በሩጫ ላይ እንዳለህ በድንገት እንዲህ ታዘግም።
በሰላሙም በትግሉም ሁሌ ታጥቀህ እንዳልነበር፣
ዛሬ ትጥቅህን ትፈታው መንገድ ጥለኸው ትቀበር።
እኔ አላምንም ይኸንን ለሰውም እንዳትነግሩ፤
ሞቷል ሲባል የኖረ ሰው አለ ሲባል ልትቀብሩ?
አብረን ስንኖር እስከ ዛሬ ያላወቅሁት ቅር ያሰኘኝ፤
ኢትዮጵያዊነትህን እንጂ፥ አማራ መሆንክን ሳትነግረኝ።
ደህና ሰንብት ኮሎኔል አለማየሁ፥ እንዳለቃ ሰላምታ
ልስጥህ፣
ደህና ክረም ጓድ አበጀ እንደ ታጋይ ልሰናበትህ፣
ለታጋይ እያለቅሱም ይላሉና እኔም አላለቅስልህ፣
እንደ ጓደኛ ሆኜ ግን መጎዳቴን ልግለጽልህ።

# ምነው ዳግም ጦርነት?

02/28/1999

የሳባ ጉዞ ምላሽ ምንሊህን ይዞ ሲተም ፣
ከፖርቹጊስ የጦር አጋር ከአሌክሳንደርያ ሥጋወ ደም
።
ከቱርክ ከድርቡሽ ወረራ ከግራኝ መሐመድ ስግደት ፣
ከቴዎድሮስ መቅደላ ከዮሐንስ የአንገት ስልበት፣
በሮም የዘርዓይ ድረስ ጎራዴ የሰላቶ ደም እልበት።
ለጣሊያን ነፍጥ በጋሻ ምትሽ፣
ጀግናሽ ከግራ ቀኝ ሲመከትልሽ።
ድል በድል ሆኖ አድዋ ላይ እልል ተብሎ ሲፎከር፣
ምነው ምኒልህ ፈረሱ ባሕር አጠገብ አድሮ በነበር።
ውጫሌ የተሻረው ውል አድዋ መፍረሱ ቀርቶ፣
አዶሊስ ላይ በነበረ ግጫ ነቅሎ ቁጤማ አንጥፎ
ውኃ ነክቶ።
ፈረንጅ በገባበት ሁሉ የተከለው ተንኮል ሴራ ፣
ለዓመታት እኛም ላይ ሊያደራ?
እንደ ቆላ ቁስል ሊነፈርቅ እንደ ነቀርሳ ሊያንሰራራ?
ከከፋሽማ ተገንጠይ ካልጣመሽ ቤታችን ቤትሽ
ባልን፣
ለትግሉ እንዳልደማን ለነሱ ትላንት እንዳልሞትን፣
ይቅር መቼስ ተብሎ የሆነ ያልሆነውን እንዳልቻልን፣
የሕዝቡን ቁጣ እንዳልገታን እሮሮውን እንዳልዋጥን፣
ሚስት እንደ ነጠቀ አጉራ ዘለል፥
ጣውንትነት ሊከጅሉን?



በጥይት ሊደበድቡን በአውሮፕላን ሊያቃጥሉን?
በሞርተር ሊጨፈጭፉን በታንካቸው ሊዳምጡን?
ተው ሲሏቸው ካልሰሙ አውራው ከሆነ ንጉሳቸው፣
ሠላም ማለት አቅቷቸው ጦር ከሆነ ዳንኪራቸው፣
ወንድሞቼ ምርጫም የለ ከንዳቸሁን አሳዩአቸው።
የተወጠረን ፊኛ እፍታ መች ይጎዳዋል፣
እስትንፋስማ ጌጡ ነው ወደ ሰማይ ይወስደዋል።
ሲነኩት ነው እንጅ በመርፌ በቢለዋ በጉጠቱ፣
የማያምረው አወዳደቁ መሽመድመዱ አሟሟቱ።
ተዋቸው ሲባሉ ከነገሱ ይብቃ ሲሏቸው ካበጡ፣
ምንም ልመና አያሻም ወንድሞች፥ የጠመቁትን
ይጠጡ።
ሰሚ ካለ ግን ጦር ይብቃ በሏቸው፥ ዘፈናቸውን
ይቀይሩ፣
«አደየ ጀጋኑ» ይቅርና ስለ ፍቅር ይዘምሩ፣
ስለሰላም ተወያዩ በሏቸው፥ መሃይሙን ሕዝብ
ያስተምሩ።
ከእጅ ወዳፍ የሚኖረውን፥ ያንን ጭቁን አርሶ አደር፣
ዛሬም ያላለፈለትን የከተማውን ላብ አደር፣
በግዴታ ተሰባስቦ የተከማቸውን ወታደር።
ምን አለ ሀሁ ቢያስተምሩት ሀ ግእዝ ለ ግዕዝ፣
የጦር ከበሮ ከመምታት፥
የትምክህት ከራር ከመጠረዝ።
ምን አለበት «አሶ» ላይ ቢረባረቡ፣
ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ቢያቀርቡ፣
ሚግ እየገዙ በየሜዳው ከሚከስሩ።
ሰውን የሚጎዳው ፍቅር እንጂ ጠብማ መዝጊያ በር
ነው፣

ትእግስት ሰላም ያዋቂ፥ ጡጫ ብትር የመሃይም
ነው።
መሪዎች ትላንት ነበሩ አልፈዋል፥ የዛሬዎቹም
ያልፋሉ፤
ምንም ነገር ቢፈጠር፥ ሕዝቦች ግን ይኖራሉ።
እናም ለማያልፈው ሕዝብ፥እትብቱን ለበጠሰ ሰው፤
ሠላምን እንስጠው እንጂ፥ ጠላትነትን አናውርሰው ።
ለምነን ለምነን እንቢ ካላችሁ ፤
ከእውነት ይልቅ የዳንዴ ውሸት ከጣማችሁ፤
ለሃገር ሳይሆን ለግለሰብ ከቆማችሁ፤
የአማባ ገነኑ ደንገጡሮች ኩርኩማችን ያውላችሁ።



# ጉንፋን

ቁልሉ አፈር ይሆን የጤፉ እብቅ ትንኝ፤
የተበከለ ዓየር የፈነዳ ቦንብ ብናኝ።
እንደ ክረምት የደጋ ኩበት ጎሮሮን የከረከረ፥
ወይ አስነጥሶ አልወጣ ወይ በስሎ አልጠነከረ፤
በለቅሶ ብሌን ጋርዶ እይታን እያሳወረ፤
የዘንድሮው ጉንፋን አንገት አስቀረቀረ።

አልቴት ወይ መድሃኒት የማይመልሰው፤
የባሕር ዛፍ ቅጠል የማይፈራ፥ አጥሚት የማይፈውሰው።
ጉልበት የሚፈታተን፥ መጋጠሚያን የሚቆረጥም፤
አፍንጫን የሚሰነፍጥ፥ የሚበላውም ነገር አይጥም።
አረጀን ጉልበት ጠፋ፤
ሰውነታችን ሲዳከም ጉንፋን በአካላችን ፎሌን ነፋ።

# ሙስና

ብል እንደ በላው ስልቻ በድንገት ከተቀደደ፣
ውሃ  እንደ ነካው ቁርበት ጠርዞን ካቆረፈደ፣
እምነት ሞራሉን አሽቀንጥሮ ሆዱን ብቻ ከወደደ።
ውሸትን እንደ ዘውድ ደፍቶ ባሉባልታ ከነገሠ፣
መልካም ማሰብ ተሰኖት ሙስናን ከደገሰ፣
ምን ቆሟል ትላላችሁ ሞቷል እንጂ በሰበሰ።

እንደ ገልቱ ሴት እንጀራ ልቡ ከቀነበረ፣
በስብእና ፍቅር ሳይሆን በቁሳቁስ ከተቀበረ።
የሥራ ባልደረቦቹን በተንኮል ከፈለፈለ፣
በተቀመጠበት በቆመበት ሰውነቱ ከቀለለ፣
መሃላውን እየሸጠ በጉርሻ  ከተደለለ፣
ምን እረጋ ትላላችሁ እንደ ማር እየዋለለ።



# እረሃብ ወይንስ ቸነፈር

የምግብ ጠረን ሲጠፋ የአቧራ ብናኝ ፊት ሲሸፍን፣
ንፋስ ካለ ቦታው አቅም ገዝቶ ገለባ፣ ጭራሮውን ሲበትን።
ዋልካ  የነበረው የእርሻ ቦታ የላመ አሸዋ ሲመስል፣
ያልተቃጠለ የሰፈር ደን ቅጠሉን አጥቶ ሲከስል።
እንስራ ጋን ማሰሮው ሳይነኩት በራሱ ሲሰበር፣
መጫኛ ከሰፈር ሲጠፋ ኮርቻ እርቃኑን ሲቀር።
የፀሐይ ጉልበት ሲጠነክር ንፋስ ያለወትሮው ሲበረታ
የሲቃ  ድምጽ ሲደራረብ ጣረ ሞት ከበሮ ሲመታ።
ይዘል የነበረ ሚዳቋ እንደ አንካሳ ውሻ ሲያነክስ፣
ጥንቸል መሮጥ አቅቶት እንደ እባብ በሆዱ ሲድበሰበስ፣
የቀንድ ከብት ሁሉን አጥቶ አፍንጫ ጉንጩን ሲልስ።
የሚሯሯጥ የሰፈር ልጅ ከቀየው መታየቱ ሲጠፋ፣
በከብት ምትክ አሞራ በአህያ ምትክ ጅብ ሲያናፋ።
አራሙቻውን ክብር ሰጥተው ወፍ ዘራሹን በጎመን
ሲተኩት፣
የደጀ ሰላም ጥጋ ጥጉን በአሬሳ ክምር ሲያስጨንቁት፣
አሃዱ የሚል ሲጠፋ መቅደሱን በሽታ ሲሞሉት።
መስጊዱ የተወረረ የተለቀቀ ቤት ሲመስል፣
አካባቢው በውሃ  እጦት በፀሐይ ሐሩር ሲከሰል።
ሰው ያገኘውን ደረቅ ቅርፊት የወደቀ አጥንት ሲግጥ፣
ለሚንቀሳቀስ ነፍሳት ላየው ሁሉ ምራቅ ሲውጥ።
መንቀሳቀስ ህልም ሲሆን እጅና እግር ሲከዳ፣
ማልቀስም ቅንጦት ሆኖ እንባም ሲደበቅ ከጓዳ።
ዝንብ ዘመቻ  ሲያውጅ ጀሬ ነጋሪት ሲመታ፣
እረሃብ ገባ ይላሉ ድርቅ ቸነፈሩ እረታ።

# ለዲሞክራሲ እንታገል

የትላንትናው የአመጽ ተስፋ በእውነታ ተቀየረ፣
የሕዝቡ ትግል ድል መታ ፋሽስቱ መንግሥት ተባረረ።
እንደ ጉንዳን አፈር ተናደ፣
እንደ ሃጥያተኛ መቃብር፣ ወደ መቀመቅ ወረደ።
ከተራበ ሕፃን ጣር ከያዘው አፍ ነጥቆ፣
እንዳልደነፋ  ባደባባይ ዛሬ ወጣ ተደብቆ።
ይኸው ሕዝቡ ድል መታ ፋሽዝም ተገረሰሰ፣
አሜፋሪው አንገቱን ደፋ ለጊዜው እፎይታ ነገሰ።
እሰየው እንበላቸው ሞተው ለገቡ ተጋዳዮች፣
እሰየው እንበላቸው ለድል ለበቁ ሕዝቦች።
ከተመታ ፋሽስቱ ትግሉ አበቃ እንዳይሉ፣
መጨቋቆን እንዳይመጣ በዲሞክራሲ እየማሉ፣
አንዱን እየደገፉ ሌላውን እያጥላሉ፣
ዝም በልን እንዳይጀምሩ ከእኛ በላይ አሳቢ እያሉ፣
ለመብት የተነሳችሁ ተባበሩና ታገሉ።
የሕዝብ ድል እኩልነት ለማግኘት ነው፣
የሕዝቡ ድል ዲሞክራሲን መገንባት ነው።
ድሉ ድላችን የምንል፣
ትግሉ ትግሌ  ብለን የምንምል።
እንማከር ጦር መስበቁን እንተውና ፣
ሲወረወር የሚሞተው ወንድም እህት ነውና።
ቅራኔ ካለ ከጦር መለስ መፍትሄ እንዲገኝለት፣
ድርጅትን የማሳሰብ ግለሰብም ግድ አለበት።
የሚከፉ ካጋጠሙን የሕዝቡ ሞት የማይሰማቸው፣
በሰላም እንቅልፍ ያጡ ጠብ መንጃ ዛሬም ያስኛቸው፣
በወላድ ስም እንማጸን ክራራይሶ  እንበላቸው።



ተነሱ አባት እናት ጦርነት የሰለቻችሁ፣
ትላንት ልጅ ወንድም እህት ጓደኛ የገበራችሁ፣
በትግል ሜዳ ባመናችሁበት የደማችሁ፣
እስቲ ይብቃን ጦርነቱ ትግል በሰላም ብላችሁ።
ሕዝቡ እንደሆን ከችግሩ ተምሯል፣
ጦርነትን እድሜውን ሙሉ ተመልክቷል፣
እየተራበ መታገልን እየታገለ መራብን ከተላመደው
ሰንብቷል።
ለግል ስልጣን አጭር መንገድ ከፋፋይ ሃሳብ ማሰላሰል፣
ይብቃ እባካችሁን እስቲ እንስከን እስቲ እንብሰል፣
ሰራተኛው አርሶ አደሩ እንደ ነቃ  እንቀበል።
ተስማምቶ መለየትን ተለያይቶ መስማማትን፣
ካለፍርሃት መቆምን በራስ እምነት መግፋትን፣
ለእውነት ለእኩልነት ለዲሞክራሲ መፋጨትን፣
በጠመንጃ  ሳይሆን በውይይት መፍታትን።
ተቃውሞ  ከሌለ እድገት፣
ልዩነት መኖሩን ካላመንን እንደማይኖር አንድነት፣
ይናገር የተማረው አንደበት።
ይችን አገር በእግሯ እናቁማት እንገንባት በጋራ፣
ከጎንደር ትግራይ ጎጃም ከሸዋ ከጊሚራ፣
ከሲዳም ከባሌ ከሐረር ከከዚራ፣
ከወለጋ ከገሙጎፋ ከኢልባቡር ከሁመራ፣
ከቢን ሻንጉል ወላይታ አሮሞ ሳንል አማራ፣
ጉራጌ ጉጂ እጅ ለእጅ ዲሞክራሲን ባንድ እንዝራ።
ለትግል የተነሳ ወጣት ትላንትና የተሰደደው፣
እስቲ ላገሩ ይብቃ የዘመድ ሰው ይበለው።
እስቲ ምሁሩ ያስተምረን እሱም ይማር ከሕዝቡ፣
ከልብ ከሆነ ጣምራነቱ ለሃቅ ከሆነ መሰባሰቡ።
እስቲ መንገድ እንሥራ ላላየው መኪና  እናሳየው፣

ት/ቤት እንከፈት እውቀትን እናስገብየው፣
ሃኪም ቤት እንገንባለት መድሃኒቱን እናድለው፣
ውሃ እንደ ልቡ ይጠጣ ጉድጓድ እናማምሰው።
ብቻ ላንከዳዳ ቃል እንግባ ጦርነትን ላናወርሰው።



# ዓባይ ደፈረሰ

6-25-1979 ካርቱም

ሸንጠ እረጅም ትልቁ ዓባይ፥
መንገደኛ የትም ሲታይ፣
በልግ መከር ከረምት ፀደይ።
ዓባይ ግንፍል ዓባይ ቁጡ፣
ዓባይ ግርማ ዓባይ ውቡ፣
ዓባይ ጥጋብ ዓባይ ቡቡ።
ዓባይ ተጓዥ ዓባይ መጭ፣
ዓባይ ናፍቆት ጥም ቆራጭ።
ጫካ ደኑን እየጣሰ፣
ጓል አሸዋ እያፈሰ፣
ይኸው መጣ ያው ደረሰ፣
ነፈረቀ አለቀሰ።
የጣና ልጁ የጎርጎራ፣
የደቀ እስጢፋው ገሞራ።
ከወይጦ ምድር እራስጌ፣
ከደሴት መሃል ዘጌ።
የሻንቅላዎች አለኝታ፣
የግሙዝ ጎጀ መከታ።
ዓባይ ግልገል ዓባይ ጥቁሩ፣
ዓባይ መውደድ ስመ ጥሩ።
መልእከተኛ ያገር ቤት ሰው፣
እንደ "ኖህ ወፍ" ብስራት ሊለው።
ያገር ቤት ወሬ ይዞ፣
ወጣ ገባውን ተጉዞ።
ዓባይ መጣ ያው ደረሰ፣

መቼ ቆመ ገሰገሰ።
ያገር ቤት ሰማይ ጥቁር ማዘሉን አበሰረ፣
የመብረቅ ጩኸት እንደ ሞላው
መሬት ቀውጢ መሆኗን ተናገረ።
በድፍርስ ዓይኑ እያለቀሰ፣
ያረጀ ግንድ ምናምኑን እየጣሰ፣
"የምስራች ወሬ ይዞ" ዓባይ ተጓዙ ደረሰ።
ዓባይ ድንበር ዓባይ ወሰን፣
ዓባይ ግርማ ዓባይ ተገን።
በየመንገድ የሞቱትን፣
አፈር አልባሽ ያላዩትን።
አስከሬናቸውን ተሸክሞ ፣
የደም ልብሳቸውን አስጥሞ ።
በሐረግ በቅጠል ገንዞ፣
በዋልካ ጭቃ "ጠርዞ"
ይዞ መጣ ሰላም አገር፣
ከሜዳ ላይ ምሶ ሊቀብር።
አገር ቤት ዶፍ እንደ በዛ ጉም ጭጋግ እንዳለበሰው፣
ማጥ ሆኖበት ተቸግሮ ገበሬው ማረስ እንዳቃተው፣
መንቀሳቀስ መላወስም ሕዝቡን እንዳስቸገረው።
የቆረጠ የደፈረ ሰንጥቆ እንደሚገባ፣
ለሚያልፍ ጅረት ሳያቅማማ ላድካሚ ማጥም ሳይባባ።
ለነጎድጓድ ለብልጭታ ለተግባብ ሳይደነግጥ፣
ለቅዝቃዜው ለውርጩ ትንሽ ፍርሃትም ሳይሰጥ።
እንደሚራወጥ አወራኝ "ዓባይ" ይህንን ተናገረ፣
አሁንም እየፈሰሰ በራሱ ቋንቋ እየዘመረ።
የዓባይ የፏፏቴው ድምጽ፣
ያባይ ያዘቅት ውስጥ ጩኸት፣
የዓባይ ፈጥኖ ኩርፍታ አትንኩኝ ብሎ መወትወት፣



የዓባይ ጉድጓድ መቆፈር የዓባይ ሸለቆ መስራት፣
ከላይ ወደ ታች መዝለል አረፋ መድፈቅ ከሳቅ ብዛት፣
የቤት ብቻ መሰለኝ ቁጣም አላየሁበት፣
ያም ቢሆን ጉልበት አለው አትቅረቡኝ አለችበት።
ዓባይ "ሰው ባገሩ" ሲል ዓባይም ቦታ ሲገዛው፣
ዓባይ አንገት ሲደፋ ዓባይም ሜዳ ሲያረጋው።
መሄዱ እንዳይታወቅ ድምጽ አጥፍቶ ሲሸመጥጥ፣
ባንድ ጎኑ እንደ ተኛ በሌላኛው ሳይገላበጥ።
የሆዱን በሆዱ እንደያዘ፣
ስንትና ስንት እንዳረገዘ፣
ፈካም ሳይል ነጎደ፣
ዓባይ ቁልቁል ወረደ።
በደረሰበት "ሊነግራቸው"
ላገኙት ሁሉ ሊያወራቸው፣
አገር ቤት ክረምቱ ከፉ ነው ሊላቸው፣
በዝናብ የረገፉ አበቦችን ሊያሳያቸው።
ዓባይ ሄደ ዓባይ ተጓዘ፣
የሆዱን በሆዱ እንዳረገዘ።
ዓባይ ተጓዥ ዓባይ መጭ፣
ዓባይ ናፍቆት ጥም ቆራጭ።
ጫካ ደኑን እያሰሰ፣
ጓል አሸዋ እያፈሰ፣
ይኸው መጣ ያው ደረሰ፣
ዓባይ ጥሩው ደፈረሰ፣
ነፈረቀ አለቀሰ።
የረሃብተኞችን የውሃ ቅል ቁርበታቸውን ተቀብሎ፣
አሮጊት ደካሞችን ሕፃን ጎረምሳን አዝሎ።
የወደቀ ምስሶ የቤት ጉልላት እየገፋ፣
ዓባይ ይዞ ደረሰ ሜዳ ሲያገኝ ሊተፋ።

ጥቁሩ ጠቁሮ ደፈራርሶ፣
ፊላ ሳሩንም ለማምሶ።
እንደ ቀብር ለቀስተኛ አቀርቅሮ ሲንቀዋለል፣
ከሌላው ጓደኛው ጋር ሊቀላቀል።
ሜዳውን እየገመሰ አሸዋ እየሰበረ፣
እንደ ዝሆን ጥርስ ተወላግዶ ቅስት እየፈጠረ።
በመደባለቁ እኮ ነው ካርቱምን ካርቱም ያሉት፣
ምስሉን ከዝሆን ጥርስ አያይዘው መጠሪያ ስም የሰጡት።
ጓደኛው ከማዶ እየሳቀ እንደ መስተዋት እያበራ፣
ሊገናኘው በምቻኮል የበሬ ሽንት እየሰራ።
በአንድ ሲቀላቀሉ አንገት ለአንገት ሲያያዙ፣
ወገብ ለወገብ ተናንቀው እርስ በእርሳቸው ሲፈዙ
የናፍቆት ሳቅና ለቅሶ የልብ የሆነ ደስታቸው፣
የዚያን ጊዜ ይሰማል ቦርጨቅጨቅ የሚል ድምጻቸው።
ትንሽ አይቆይ ብዙም አይፈጅ፣
ሁለት ዓባይ በአንድ ወራጅ።
የዚህ ለቅሶው አስለቅሶት፣
ነጩንም እንባ አደፍርሶት።
የሚያበራ መልኩ ተለውጦ፣
በድፍርስ እንባ ተውጦ።
ማን ሊያውቅና ሊለያቸው፣
ሁለት ዓባይ አንድ ናቸው።
ዓባይ ተጓዥ ዓባይ መጭ፣
ዓባይ ናፍቆት ጥም ቆራጭ።
ጫካ ደኑን እያሰሰ፣
ጓል አሸዋ እያፈሰ፣
ይኸው መጣ ያው ደረሰ፣
ነፈረቀ አለቀሰ፣
ነፈረቀ አለቀሰ።



# ዘመን

የዓመት ድምር የእድሜ ሙላት፣
እጣ ክፍሉን እየለያት፣
ትዝታውን እየረሳ የትላንቱን ሲያዳፍናት።
ልጅነቱን ለማቅረብ ሽበቱን እየደበቀው፣
ተፈጥሮ ግን እንቢኝ ብሎ ደም ብዛቱን እያሞቀው፣
ሐዘን ልቡን አደንድኖ ጭምታን እያደለው።
መቻቻልን አከናንቦ እይታውን እያሰፋ፣
በትእግስት እየቀዘፈ ማድመጥ ለምዶ ሳይደነፋ።
ተበትኖ እንደ ጤፍ ዘር፣
ባሕር ማዶ ልውጥ ሰፈር፣
ተሰብስቧል ዓመት ቆጥሮ ስለ ጤና ሊነጋገር።
ቤተሰቡን ሊያስተዋውቅ ልጅ ከልጁ ሊያፈቃቅር፣
ያላለቀ ያልተቋጨ የዓመት ወሬ ሊያጠናቅር፣
የጠፋ ሰው ሊያፈላልግ ሞተ ሲሉት ሊያቀረቅር።
ተሰብስቧል የአምና ተኳሽ እንደ ኩፉፍ ካሜራ አዝሎ፣
ኮት ጃባውን አጥልቆ ከራባቱን አንጠልጥሎ።
ያለበትን ልትጠይቀው ያለችበትን ሊጠይቃት፣
ስለ ማግባቱ ልታዳምጥ ልጆቿን ሊስምላት፣
ያለፈ ታሪክ ሹክ ብሎ አስገንፍሎ ሊያሳስቃት።

ያ ልጅነት ዛሬ ቀርቶ፣
አትንኩኝ ባይነቱ ተረስቶ፣
እንዳላስፈራራ በሰው ሃገር ሕግ ፈርቶ።
ግማሹ መስቀሉን አስሮ ገሚሱ መስገጃ አዝሎ፣
ለነጻነት ያለ ተጋዳይ ልጆቹን በቤት አጅሎ።
እንዳይጠፉበት ቆልፎ፣

ወጡ ሲሉ ተንዘፍዝፎ፣
አለ  ያ የትላንት ተጋዳይ ፍርሃትን በኑሮ  ታቅፎ።
መጠሪያም የለው ያስቀመጠው፣
እድሜውን ቆርጦት ሳይጨንቀው፣
ቢኖርም ቀኑ እራቀው።



# ሕብስቱ[10]

ውጥንቅጥ ላይ ታትሞ  የነበረ

ከበነነ  ዱቄት ተላቁጦ፣
እርሾና ውሃው ተቀይጦ።
ከታፈነ የኩበት ጭስ፣
ከተወቀጠ የጥፍጥሬ እብስ።
በወፍ ዘራሽ እንደኋሁላ ተሸፍኖ፣
ወይ በኮባ ተሸሞንሙኖ።
ካልሆነም በሙዝ ቅጠል ታጅሎ፣
የብረት ምጣድ ካናቱአዝሎ።
ካጋመ የወይራ ንዳድ፣
ከፋመ የሸክላ ምጣድ።

ከጉልቻ ምሽግ አናት ተፈናጦ፣
በለስላሳው ገላው እሳተ እሳት እረግጦ፣
ልስልስ ሙናውን ለውጦ።

ፊቱን ኮስትሮ፣
ልል ገላው አደንድሮ፣
ከተኛበት ተነስቶ፥
ኩፍ እንደ ነብር ውሻ  እንዳስተዋለች ቀበሮ።
ቅመሙን እንዳጨቀ ሳይተፋና ሳይበትን፣

10 የ ፺ አለቃ ሕብስቱ የደርግን መንግስት በመቃወም አምጸው ከወጡት የአየር ወለድ አባላት አንዱ ነበር። እንቅስቃሴውን በመደገፍ ብዙ አስተዋጽኦ ያበረከተ ቆራጥ ደፋርና ንቁ ወንድም ነበር። የኢሕአሰ ሰራዊት ውቅሮን ለማጥቃት ባደረው ውጊያ መቁሰሉን ሲረዳ ምሽግ ዘሎ በመግባት በጨበጣ እየተናነቀ የተሰዋ ደፋር ጀግና ነው።

ኩምትር ድርቅ በቅጠል ግናዝ፣
ከታች ከላይ ባለ ወላፈን።

ወጣቱን ሊስብ ልጆች ሊማርከ፣
በአዛውንት ሊመሰገን በቄስ ሁሉ ሊባረከ፣
በሆያ ሆዬ መዝሙር ሊታከክ፣
በተፋቀ ባልተፋቀ ጥርስ ሊታኘክ።

በከርሰ ሰብአ ሊታነቅ፣
በጠወለገ ምራቅ ሊጨማለቅ።
በአቃቢት ቀሚስ ሊሸፈን፣
ለጠበል ጠዲቅ ሊበተን።
የድሮው ታናሽ ሙልሙል አንቱ፣
የቡሄ በሉ የጥምቀት ቤቱ፣
የልጅ መከሰሱ የአዋቂ እራቱ፣
እየቆየ አገረሸብኝ ትዝ ይለኝ ጀመር ሕብስቱ።

***ለ ፶ አለቃ ሕብስቱ***
***መታሰቢያ***



# [11]ሥጋም በቁሙ ሲከዳ

ብርታትማ በጤና ነው፣
ጉብዝናማ ሲላወሱ ነው።
የሚከብደው እጣ ሲከዳ፣
የሚመረው አካል ሲጎዳ፣
የሚያስለቅሰው ደም ሲቀዳ፣
ሥጋም በቁሙ ሲከዳ።
የአነገበከው ጥይት ሲከብድህ፣
የያዝከው ዝናድር ሲከድህ።
የሮጥክበት እግርህ ሲጠፈር፣
የተኮስክበት ጣት ሲታሰር።
ወገብህ መጥናት ሲያቅተው፣
አንገትህ ትራስ ሲርቀው።
ሥጋም ባዳ አይደል ጥንቱን፣
የአሁን እንጂ አያይ የፊቱን።
ላንቃህ ትናጋህ ሲደርቅ፣
ሳንባህ ሳል ያለ ወትሮው ሲሰርቅ።
ያን ጊዜ ነው እውነትም ብስጭት፣
ያን ግዜ ነው እውነትም ንዴት።
ያትንኩኝ አንባህ ሲደፈር፣
ሥጋህ እንደ ድርቆሽ ሲፈረፈር።
አጥንትህ ቅንቡርስ ሲሰራ፣
መኝታህ ደን ሲያደራ፣
ቁርበትህ ዝንብ ሲጠራ።

[11] ጌትነት ጋረድ የደርግን አገዛዝ ተቃውመው ከወጡት የአየር ወለድ ወታደሮች አንዱ ሲሆን የኢሕአፓን ሰራዊት በመቀላቀል በትግል ላይ የነበረ ነበር። የሃይል 500 መሪ ሆኖ የውቅሮን ከተማ ለማጥቃት በተቀየሰ ውጊያ ላይ ቆስሎ ሲታመም ከቆየ በኋላ ሕይወቱ አልፏል። ጌትነት ትሁት ደግና ቆራጥ ወንድም ነበር።

ያኔ ነው እውነትም ጣረ ሞት፣
ያኔ ነው የሲቃ እግር ብረት።
ብቻ ቀን ጨለማ ነው ላላየው፣
ጣራ አይታውን ለጋረደው፣
እግሩን ለሸነከለው፣
እንቡርታውን ለነጠቀው።
አሞቱን ላፈረጠበት፣
ተስፋውን ላጨለመበት፣
ቀኑና ለሊቱ ምን ልዩነት አለበት?
ያመንከው ሲከዳ፣
ቁመናህ ሲሆን ባዳ።
ጓደኛህ ዓይንህን ሲጠየፍ፣
ቆዳህ እንደ እባብ ሲገለፈፍ።
በርታ ሲሉህ በርትተህ፣
አታቃስት ሲሉህ ታመህ።
የሚረዳህ ሰው ስታጣ፣
ቆዳህ ቀለሙ ሲገረጣ፣
አጥንትህ ከከርታሱ ሲወጣ።
ያን እለት ነው እኮ ሞትህ፣
ቁጣህና ቁጭትህ፣
የዋይ ነዶ ፍም እንፋሎትህ፣
የሚለበልብ መፋጀትህ።
ላንተ ለጓደኛዬ ሴኮንድ እርቃህ፣
ደቂቃ እንደ ሕልም ታይታህ።
ያየህው ሕልም ተበላሽቶ፣
አለ መከረምህን አይቶ።
ትንፋሽህ ጠረኑ ተለውጦ፣
እግርህ እንደ ደጋን ጎብጦ።
እጅህ እንደ አገዳ ደርቆ፣



አካልህ የያዘውን ለቆ።
አውቃለሁ ያኔ ነው ሞትህ፣
በውዳሴ አይሸኝግሉህ፣
በመዝሙረ ዳዊት አይጠግኑህ።
መስንበትህን እየጠሉ፣
የመቃብር ቦታ እያሰሉ።
መሞትክን እየጠበቁ፣
የፈውሱን ብልሃት እያራቁ።
ስታይ ያኔ ነው የሞትከው፣
እንደፈረዱብህ ያወከው፣
ያኔ ነው መሰዋትህን የተቀበልከው።

*ለ ፲ አለቃ ጌትነት ጋረድ*

# መገዘዝ

በውጥንቅጥ ላይ ታትሞ  የነበረ

መገዘዝ ትንሽ መገዘዝ ጫንቃ፣
መገዘዝ ድንጋይ መገዘዝ ሳንቃ።
የኮረማሽ የማዶ ቃፊር የጠራ አጎጠጎጤ፣
የአንኮበር ቁንዲ ምስያ የወሲል አፈ ቀላጤ።

የአሳግርት የሸንጎ በትር የሙገሬ ዛላ አፍንጫ፣
የውርጭ የቁር የንፋስ መውጫ።

የጊናገር የኋላ ግድ የኮቱ ገበያ ሰዓቱ፣
ጥላሽን ካላዩ መሸ አይሉ ሸቀጣ ሸቀጣቸውን
አይከቱ።

እናትሽ ካልጠቆረ ዝናብን አይተነብዩ፣
መንገዳቸውን አያውቁ ቀና ብለው አንቺን ካላዩ።

ሰሜን ደቡብ ምልከት ምዕራብ ምስራቅ ችካሉ፣
አንቺ ነሽ አሉኝ መገዘዝ የምንጃር ቡልጋ መሃሉ።

መገዘዝ የዳሳ አገር፣
መገዘዝ የብርድ መንደር፣
መገዘዝ ቋት መገዘዝ የድንች ሰፈር።
የሞቷል ቅበሩ ጥሪ የጦርነት መጣ ማማ፣
እናቷን እንደ አረብ ሴት በተሳቢ ጉም አጨልማ፣
ደረቷን በአለት አሽለምልማ፣



ጥዳን በዳሳ አስከብባ በጦስኝ አውድማ ፍማ፣
ለአፈ ታሪክ ምስክር መንገድ ለጠፋው ዋቢ ቆማ፣
ወባ የጣለውን ቆለኛ በጦስኝ ጠቦት አስታማ፣
በበጠጥ በኩበት እሳት አፍማ፣
አለች ዛሬም አገግማ።

መገዘዝ የቡልጋ ቁንጮ ያናቱ፣
የወሲል ግድ ማጅራቱ።
የሾላ ገበያ አድባር፣
ያሳግርት የፊት ግንባር።

የላሎ ምድር ጉልህ ዓይኑ፣
የአንኮበር የኋላ ደጀኑ።
የተጉለት ጠንካራ አጥሩ፣
የጅሩ ካሰማ ምስማሩ።

መገዘዝ የደበሎ ሃገር፣
መገዘዝ የግዞት መንደር።
መገዘዝ ጦስኝ መገዘዝ ዳሳ፣
ትላንት ቴዎድሮስ ስምሽን ሲያነሳ፣
አጠገብሽ ቢሆን ኖሮ ለፈረንጅ እጅም ባልነሳ፣
ሽርተት ይል ነበር ሙገሬ ከሰም ከዱር ሆኖ  ሊያገሳ።

# ጦርነት

ጉልበተኛ የፈጠረውን መጋፋት ለመደምሰስ፣
ስብእናውን ለማውደም ሥጋውን ካፈር ለመመለስ፣
የሚጨሰውን ቤት ለመዝጋት ለሽረሪት ለመለገስ፣
በጫወታ  ዘፈን ምትክ እሮሮ  ሐዘን ለመደገስ።
አባት እናት አልባ ሕጻን በሰፈሩ ለመጨመር፣
ሰውን ገድሎ  ለመደሰት ፍጡር ጥሎ ለመፎከር።
ሳቂታ ጥርስ ለማደብዘዝ የቆመውን ለማንበርከክ፣
ሁሉን ጥፋት በሟቹ ላይ ለመቆለል ለማላከክ፣
የሰው አንገት እንደ ዶሮ ለመቅንጠስ ለመባረክ።
በመግደሉ ለመመረቅ በማቁሰሉ ለመሸለም፣
ይህ ነው ጦርነት ውጤቱ ጨካኝ እንደ እርሱ በዓለም
የለም።
የስልጣኔ  መቃብር ቆፋሪ የእድገት እንቅፋት መሰናክል፣
የድንቁርና በር ከፋች የርሃብ ችግር መደላድል፣
ጦርነት ነው የጥፋት ወንድም ጦርነት ነው የሕይወት
ቁስል።
ልዩነት የማይገባው  ባለ ጡንቻ ጉልበተኛ፣
ምን እውነት ጠላቱ ቢኖረው እሱ ካልገነነ የማይተኛ።
ጆሮው የደነቆረ የሚነገረውን የማይሰማ፣
በሰለባ ካልሆነ በውይይት የማይታማ።
ማፈራረስን እንጂ መገንባትን የረሳ፣
በቆመው የሚፎከር በወደቀው ላይ የሚያገሳ፣
ለምስክርነት ቆጣሪ ምርኮኛ የተከመረ እሬሳ፣
ጦርነት ነው ላንዱ ኩራት ላንዱ ችግር አበሳ።



# [12]የገደሏችሁም ሞቱ

መተንፈሳችሁን ያልወደዱ መታገላችሁ ያስፈራቸው፣
ጅምራችሁን የተረዱ እድገታችሁ እንቅልፍ
የነሳቸው።
ከመሃል ከውስጣቸው የጉያ ትኳን ሆናችሁ፣
ቅስቀሳን ማደራጀቱን በግል በተናጠል ተምራችሁ፣
የሚበተኑ ጽሑፎችን ሌሊት እያተማችሁ፣
እንዳዲስ ተሰብስባችሁ፣
ጠዋት "ወይ ጉድ" ያላችሁ፣
እንደ ድግስ ድፍድፍ ጣይ የራሳችሁን ቀማምሳችሁ፣
የጭቁን ወታደርን አመጽ ባየር ወለድ የጸነሳችሁ፣
እርግዝናው ሲታወቅ ሜዳ  የዘለቃችሁ፣
በትግል ትንንቅ መሃከል በሞት የረገፋችሁ፣
ምን ብትለዩን በድንገት ከሙታን በላይ ነው
ሥራችሁ።
አልረሳም መልክህን ጭራሽ ወንድም አገኝ ብለው
ባይጠሩ፣
አልዘንጋም ቁመናህን ግርማ በልሁ ብለው
ባይመሰክሩ።
እኔስ ዋቢያችሁ ልሁን ላመጻችሁ ለእንቢተኝነት፣
አሻፈረኝ ለፋሽስት ላለ ክንድ ቃሉን በሞት
ላተመበት።
ምስክር ነኝ በቆራጥነት ለመውደቃችሁ፣
በጥይት ተመታችሁ፣

[12] ወታደር ወንድም አገኝ ብርሃኑና ወታደር ግርማ  በልሁ በአየር ወለድ አመጽ ግንባር ቀደምት ሚና  የተጫወቱ እኩሪ ወንድሞ ች ነበሩ። ሁለቱም ከደርግ ጋር በተደረገ ውጊያ  ላይ ተሰውተዋል።

በሞርተር ፈንጂ ተበጣጥሳችሁ፣
ምስክር ነኝ ለሕዝብ መብት እራሳችሁን
ለመስጠታችሁ፣
ምስክር ነኝ ለጭቁን ሕዝብ ግርማ ወንድም
ለመሆናችሁ።
"እንፈራም ሞት ገዳዮች ይረግፋሉ፣
እንበረከክም ለጠላት በትግላችን ይወድማሉ።"
ያላችሁት ትንቢት ደረሰ፣
የገዳዩ ቤቱ ፈራርሰ።
ያሳደዳችሁ ተሳዶ ቃሊቲ ገብቶ መሸገ፣
ደፋር ነኝ ያለው ፈሪ ካገር ውጭ አፈገፈገ።
ገዳይ የነበረው ሞተ ገራፊ የነበረው ታሰረ፣

ቀይ ሽብሩ በእናንተ በመሰሎች ደም ተቋጠረ፣
የጥጋበኞቹ ልብ ተረታ አብጦ የነበርው ተሰበረ።



# ለፋሲካው ምን ታረደ?

ክርስቶስ ለኛ ሲል ተሰቅሎ ሐጥእን ነፃ ሊያወጣ፣
ሞትን ዝንተ ዓለም ሊገድል የመንፈስ ፀጋን ሊያጠጣ።
ለጠፋው በግ አስቦ ሊጣራ በእረኛ ምልከት፣
ተዘግቶ የነበረውን የመንግስተ ሰማያትን በር ሊከፍት።
በእርሱ መከራ ስቃይ ሰይጣን መቀመቅ ሲገባ፣
በፈሰሰው ደሙ የደህንነት ድልድይ ተገነባ።
ይህንን መታሰቢያውን ለማክበር ለቆማችሁ፣
፶ ቀን በጾም ሰንብታችሁ ለትንሳኤውን ለደረሳችሁ፣
ያገር ቤት ዘመዶቼ እንኳን ጾሙን ፈታላችሁ፣
ለመሆኑ ለፋሲካው ምን ፍሪዳ ጣላችሁ?
ስንት ተሸጠ አንድ ዶሮ? ስንት ተሸጠ ሙክቱ?
ምን ታረደ ዘመዶቼ ምን ወደቀ በየቤቱ?
ስሞት ንገሩኝ ለፋሲካ ምን በላችሁ?
አስፋልት ለብለብ እንዳትሉኝ የድሮውን አስታውሳችሁ።
ካልሆነ በመንፈስ ብቻ ተሞላችሁ?
የእርሱን መሰዋት ተሰብስባችሁ አሰባችሁ?
ለሁሉም ነገር ፍሪዳ ለጣላችሁ፣
ዶሮ ቅርጫ ላረዳችሁ፣
በግ ለታሪክ ለተዋችሁ፣
ሙክት ላደለባችሁ፣
ጾሙም አልቆ በተልባ ለገደፋችሁ፣
ለክርስቲያን ዘመዶቼ እንኳን ጾሙን ፈታላችሁ፣
በፍቅር በጤና የዓመት ሰው ይበላችሁ።

# ዝምታህን ፈሩት

የፈላ የዶሮ መላጫ ውሃ፣
የተጠረበ ድንጋይ ቅርጽ ያወጣ ብሃ።
የቀና ወራጅ እንጨት፣
ዓይን ጉብጠት የሌለበት፣
ግንባሩን ሰጪ ላመነበት፣
ፍርሃት ልምምጥ ያልሰራበት፣
ምነው ትናጋህን?
የሚፋጅ ትንፋሽህን
የጠላ አተላ ሞሉበት።

ጡንጫህን አይተው ፈርተው፣
በጀግንነትህ ተደናግጠው፣
ሥር ምሰው ቅጠል ቀጥቅጠው፣
ይግባኝ በሌለው ሸንጎ ወስነው፣
ብናኝ ዋንጫህን አስነክተው፣
ሕይወትህን ፈረዱባት ጨክነው።

ምነው ጀግንነትህን ደበቁት፣
ባልታወቀ ድፍድፍ ሞሉት?
በመርዝ እድሜህን ቀጩት፣
በዱር በገደል ያልቻሉትን በዋንጫ ጠላ ፈተኑት፣
የደረትህን ደም አፈሉት፣
እይታህን ጋረዱት፣
ገመድ የለመዱ ጣቶችህን በፈትል አስረው አሸነፉት።



ምነው ታዬ ቶላ ሳትዘጋጅ የእድሜህን ጀንበር
አጨለሙት፣
የትግል ተስፋህን አሰጠሙት፣
ያንቀጠቀጥ የነበረውን ቁመና አስተኙተውም ፈሩት፣
በዝምታህ ተደናግጠው ሸሹት፣
አሬሳህንም አላመኑት፣
እንዳይዛቸው እራቁት።

*ለ፲ አለቃ [13] ታየ ቶላ*

13 የ፲ አለቃ ታየ ቶላ የአየር ወለድን አመጽ ከመሩት ቆራጥ ታጋዮች አንዱ ነበር። በትግል ሕይወቱ ሁሉንም ያስደሰት የነበረ የማይረሳ ትዝታ ጥሎ ያለፈ ታጋይ ነው። ታየ የታወቀ ኮማንዲስ ብቻ ሳይሆን የታወቀ አሰልጣኝም ነበር። ታየ ጭልጋ ላይ ተሰዋ።

# ሰው ጠፋ

ሚዛን መዛኝ እውነተኛ፣
ሳያስማማ የማይተኛ።
የሚደሰት በወንድም ሥራ፤
የሚረካ በህቱ አዝመራ።
ቅን አሳቢ የእምነት ጌታ፣
ባአሉባልታ የማይፈታ።
ነገሮችን የማይበልት፣
ቅንነትን የማይሸልት።
ደግ አሳቢ ትክሻ ያለው፣
ንገሩኝ የትኛው ሰው ነው?
እርህራሄአችን ተደፋ፣
ልባችን በነገር ሰፋ፣
የልዩነት አከንባሎ ባናታችን ተንሰራፋ።
ጭካኔን የሙጥኝ ብለን ያዝን መናናቅ በላያችን አናፋ፣
ወንድም እህት ማለት ቀረ የሚከባበር የሚዋደድ ሰው
ጠፋ።



# ዓባይ ልገደብ አለ

የዓመታት ጉዞ ታሪኩን ለቅሶውን እያስታወሰ፣
ወላጁን እየናፈቀ ዝንተ ዓለም እየፈሰሰ፣
የተራራ ላይ ስንቁን አፈሩን፡ እየገመሰ፣
ለወገቡ መደገፊያ ዛፍ ምርኩዙን፡ እያጋበሰ፣
ዓባይ የጣና ውልዱ ጎረቤት አገር ገሰገሰ፣
እረጅሙን ጉዞ ተያያዘው ላይመለስ ቁልቁል ፈሰሰ።
ስደተኛው ጥቁር ዓባይ ወደ ካርቱም አመራ፣
የግብጦችን ውሃ ጥም ሊቆርጥ ከተማቸውን ሊያበራ፣
ለራሱ ሰቀላ ሳይኖረው ለባእድ እልፍኝ ሊሠራ፣
የዘመድ እረሃብ እረስቶ ለውጭ አዝመራ ሊዘራ።
ዓባይ የማያረጅ ዓባይ የጣና ጎረምሳ፣
ከእንቅልፉ ነቃ ልበል ዛሬ? ዘመድ ብሎ ተነሳ።
ሳትበሉ አላበላም ብሎ፣
ቤቱን ሳያሸንፍ ጎረቤት ላይጋብዝ ምሎ።
ተነሳ ዓባይ ኩሬ ሊሠራ ለጎረቤት ያደረገውን ሊደግም፣
በግድብ ድልድይ ውስጥ አልፎ አሁንም ወደፊት
ሊያዘግም።
በመስኖ እያዳረሰ አካባቢውን አጠጥቶ፣
ደህና ሰንብቱ ሊለን ላገሩ ብርሃን አብርቶ።
ዓባይ መንገድ ለጠፋው መሪ ዓባይ የማይመጣ ሰው፣
መሄዴ ካልቀረ ብሎ መንደር ሰፈሩን አቃመሰው፣
ወገቡን ሸብ አድርጎ ብርሃን ሞገሱን አላበሰው።
በነፃ ሲጋብዝ እንዳልኖረ ዛሬ ዘመዶቹን ናፍቆ፣
ከፈኋቸው ማለት ጀመረ በችግራቸው ተጨንቆ።
እናቱን የማይረዳ ልጅ እርግማን አለበት ብሎ አምኖ፣

ከውጭ የመጣ ገንዘብ ሳይኖረው በዘመድ ቤተሰብ
ተማምኖ፣
አገሩን ሊረዳ ተነሳ በግድብ ሊያልፍ ወሰኖ።
መሄዱ ካልቀረ ልስጣችሁ አለ ያለኝን ላካፍላችሁ፣
አልመጣም ዳግም አንተያይ ተርባችሁ ግን አልተዋችሁ፣
ተጓዥ ነኝ አልሽከረከር ተጠምታችሁ አላልፍ ትቻቺሁ።
መረዳዳቱ መልካም ነው አለ በልጅ አዋቂው ኮርቶ፣
ዓባይ ለልማት ተነሳ በዘመድ እውቀት ተመክቶ። ዓባይ
የምዬ ኢትዮጵያ ለቅሶ፣
ዓባይ የጣና ምሰሶ፣
ዛሬ ድንገት ባኖ ተነሳ ለዘመናት በነፃ ፈሶ።
የተንጣለለው ዓባይ የሱዳን የግብጥ ደመራ፣
ፊቱን መለሰ ዛሬ ባገሩ ቤት ሊሠራ፣
ዘመድ አዝማድ ወላጆቹን ካጽናፍ አጽናፍ ሊያኩራራ!!
በቁርጠኛነት ተነስቶ ዓባይ በቃኝ ልገደብ አለ፣
ለሁሉም እንደሚበቃ ላመነው ሁሉ እየማለ፣
ላሳደጉኝ ዋጋ ልከፈል ላጠቡኝ ላጥባቸው አለ።



# ሕግ በምህረት ሲሸፈን

አመድ የሸፈነው ፍም እናቱ የደረ ቁስል፣
ላዩ የቀነበረ ዳቦ ያልበሰለ ግንፍልፍል፣
ተበልቶ ጤና ሊነሳ ሲነካ ቆይቶ ሊያቃጥል፣
ብሰና እየተነነ ጋዝ እየፈጠረ ሊበክል።

የረገጠውን ሊያንገበግብ  የጨበጠውን ሊለመጥጥ፣
እንኳን ለዓይን ምስክር ለሰሚ ሁሉ ሊሰነፍጥ።
በምሕረት ካባ ላይሸፈን በፍቅር በርኖስ ላይቀበር፣
በእምነት ጥላ ላይጠለል በይቅርታ ላይታጠር።
ስሙ ተቀያይሮ ገዳይነቱ ባይወሳ፣
ዓመታት ቢያልፉም ግፍ መሆኑ አይረሳ።

ካሚሚትም አሚሚት ብልት አካሉ ተቆርጦ፣
በፈላ ዘይት ተጠብሶ በሽቦ ባለንጋ ተለምጥጦ።
ዓይኑ በጉጠት ወጥቶ ጥፍሩ በወረንጦ ተነቅሎ፣
በጉድጓድ ተወርውሮ በከምር እሬሳ ተጠቅልሎ።
ለተሰዋ ወጣት ካልቆምን በግፍ ለተገደለ፣
ትግሉ ምኑን ትግል ተባለ።

ምንድነው እሱ ምሕረት እጁ በደም ሲበከል፣
የእናት ለቅሶ የአባት ሐዘን ወይኔ ልጄ ሲከለከል።
የት ነበሩ አባቶቹ? ሰበካን ዛሬ የጀመሩን፣
ሲገድሉ ሳይተነፍሱ ምሕረትን የሚያስተምሩን።

ገዳዬቹን ትናንት እንደፈሯቸው፣
ዛሬም መታሰራቸው ከበዳቸው፣
አንቱ ባሉበት አፋቸው አንተነታቸው  ቀፈፋቸው፣
በሞቱት ላይ ፈረዱና ገዳዬቹን አስለቀቋቸው።

መንግሥትም  መመሪያውን አጎበጠ፣
እስረኞቹን በጓሮ በር አስመለጠ።
ተቃራኒ ሃሳብ ፈጠረ፣
ገሚሱን በሕግ ጥሰት ከርቸሌ ልኮ አስኮብልሎ፣
ከምንም በላይ ደንብ መከበር አለበት ብሎ፥
ዛሬ ገዳዮችን ከፊታ ሕጉን እያፈረሰ፣
ምን መመሪያ ሆነ ቃሉን በቃል ከቀለበሰ?
ምን ሕግ ሆነ ሲጠቅም የሚጠቀስ?
ካስፈለገ  የሚጣመም እንዳሻ የሚቀለበስ።

እኔስ አልማርኩም አይማረኝ የወንድም ደም አለብኝ፣
ይቅርታ የለኝም ለፋሽስት ጨካኝ ብላችሁ ፍረዱብኝ።
እኔስ አልምርም አይማረኝ የእህቶቼ ደም ሳይመለስ፣
የእናት ያባት የግፍ ለቅሶ ኤሎሄው ሳይታበስ፣
የሙት ፍትሃት ሳይደረግ ባጎበር እንኳን ሳይለቀስ፣
አልምርም የወንድም የእህት የአባት የእናት ደም
ሳይመለስ።
አልምርም......................................



# ለማረሱስ እደርሳለሁ

የሙት ለቅሶ የአባት እርግማን፣
የችግር ምጽዋት የነፍስ ይማር እርጥባን፣
ሲያፋቅረን ሲያስማማን፣
ለስካር ብር ስንመነዝር እራት መጋበዝ ሲያስጠላን፣
ለመቅበር ስንሽቀዳደም በሕይወት መክረሙ ሲያባላን፣
በቁም ሳንረዳዳ ለሞት እንባ ሲቀዳን።
በመውለዱ ስንናደድ መማሩን ስናናንቀው፣
በመደሰቱ እንደመፈንደቅ ልፋቱን ስናንቋሽሸው።
በማወቁ የምንቆጭ በባለማወቃችን የምንኮራ፣
ምንድነን እኛ? ያረም እርሻ? ያሽዋላይ አዝመራ?
ምንድነን እኮ? መከር ጠባቂዎች ሳንዘራ።
እኮ ምንድነን እኛ?
ቀላድ የሌለው መልከኛ፣
ከብት የሌለው እረኛ፣
ድንኳን ዳስ ያልጣለ ሠርገኛ፣
እኮ ምንድነን እኛ?

ሳንስማማ ለሰላም ቆመናል የምንል፣
ጠብ መንጃ  የሌለው ተኳሽ በሕልም ሁሉን የምንገድ።
ከችግኝ በፊት ዛፍ የምንመኝ፣
ለግንባታው የምንደበቅ ለማፍረሱ የምንገኝ።
ነፍሰ ጡር የምንጠላ ለማስጨንገፍ የምንጥር፣
ለማስወረድ መላ የምንፈጥር።

ምንድነን እኛ?

አብሮ መነሳት የተሳነን፣
አብሮ መውደቅ ያስተባበረን፣
እረሃብ ልመና ያፋቀረን፣
እኮ ምንድነን?

እኔም አውቃለሁ እናቴ በእርግዝናሽ አደጎምኩም፣
መውለድሽን ስለምቀበል አስወርጅውም አላልኩም።
ያሁሉ አለፈ የእኔ እናት ለመጭው ግብ ቃል ልግባልሽ፣
በርግዝናው ባልራዳ እመጫት ነሽና ላርስሽ።
ያከፋይ አደለም መች ገደፍሽና ልጆችሽ እንዳይራቡ፣
ትልቆቹን አስተባብሬ ዳቦ ላቅርብ ጠግበው እንዲመገቡ።

ድህነትና እረሃብ መለያሽ ሆኖ እንዳይቀር፣
የተጀመረው የልማት ማገር ይጠናከር፣
የኩራዝ ብዥታው ይቀየር ጨለማው በብርሃን ይሰበር።
ልጆችሽ ጠግበው ካደሩ፣
ጠዋት በተራቸው ያስተምሩ፣
የሚስማማቸውን የሚፈልጉትን ይናገሩ።
እኔ በእኔነት ቃል ልግባ ዳግም፣
ባቅሜ ለረዳሽ ወገብሽ እስኪያገግም።
ሞትሽን ላልመኝ፣
በችግርሽ ላልቀኝ።
ቃል ልግባ ዳግም፣
ልረዳ ወገብሽ እስኪያገግም፣
ቃል ልግባ ዳግም።



# የመውደድ ጋሬጣ

ወንድምሽን የጠላሁት፣
እናትሽን የረገምኩት፣
አባትሽን የናቅኳቸው፣
አክስትሽን የራቅኳቸው፣
በእሳታችን ውሃ አፍሰው፣
በፍቅራችን ተፈላሰፈው።
በመውደድሽ ተለብልበሽ በመውደዴ ገላምጠውኝ፣
እንደ በረት ገልባጭ ዳንዴ አመናጭቀው አንጓጠውኝ።
በፍቅራችን ተቀላልደው፣
እኔነቴን በማቃለል አንችነትሽን አዋደው።
ምን አገኙ ዘመዶችሽ ሰዓታችንን የተሻሙን?
ብቻችንን እንዳንሆን ተከላከለው ለዓይኔና ለዓይንሽ ዘብ የሆኑን?
"ቅና ያለው............. " ቃል ሊፈጸም የምሳሌ ቋጠሮ፣
እርምጃሽ በፈቃድ ተከልክሎ አይታሽ በግልምጫ ታስሮ
።
አልጋሽ እንደ ህሙም ተዳብሶ ፣
መተኛትሽ ለቤተሰብ ተዳርሶ ።
ወጣ ስትይ ቤቱ ተጨንቆ ፣
ስትመለሽ ተፈንድቆ ።
ምን አገኙ? ዘመዶችሽ ሰዓታችንን ተሻምተው?
ዓይኔን ዓይንሽ ውስጥ እንዳላይበት ጋርደው፣
ምን አገኙ? ብቻችንን እንዳንሆን ተከላከለው።